ዲፓርትመንት ኦፍ ሞተር ቪክልስ

DISTRICT OF COLUMBIA

የሞተርሳይክል መማሪያ

ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ
ዲፓርትመንት ኦፍ ሞተር ቼክልስ
የሞተርሳይክል መንጃ መማሪያ

በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሞተርሳይክል ለመንዳት ከፈለጉ ህጋዊ የሞተርሳይክል መንጃ ፍቃድ(M) መያዝ አለብዎት።
የዲሲ ህግ ሞተርሳይክልን 2 ወይም 3 ተሽከርካሪ ያለው ብሎ ሲገልጸው ፡ ከሚከተሉት ውስጥም አንድ ወይም ከዚያ በላይ ባህሪያት አሉት፡

- የፒስተኑ ሽፋን ከሓምሳ (50) ኪዩቢክ ሴንቲሜትር በላይ የሆነ።
- በውሀ ልክ መሬት ላይ ከ35 ማይልስ በሰዓት በላይ መጓዝ የሚችል።
- ከአንድ ከግማሽ (1.5) የማቆም የፈረስ ጉልበት(በኤስ.ኤ.ኢ.)መለኪያ ያለው።
- ተሽከርካሪዎቹ ከ16 ኢንች በታች ዲያሜትር ያላቸው።
- ማኑዋል ትራንስሚሽን ያለው።

<u>ማሳሰቢያ</u>: ያልዎት ባለ 2 ወይም 3 የሞተር ተሽከርካሪ ከላይ ከተጠቀሱት 5 ባህሪያት ምንም ከሌለው የሞተር ቢስክሊት በሚለው ስር ይካተትና ጊዚያዊ የመንጃ ፍቃድ ባለው ወይም የመንጃ ፍቃድ ባለው ግለሰብ ሊነዳ ይችላል ። (ተሽከርካሪው ኢንስፔክሽን ስለማለፉ ፣ መመዝገቡ እንዲሁም የመድህን ዋስትና ማቅረብ ያስፈልጋል) ።

ባልዎት የዲሲ የመንጃ ላይ የሞተርሳይክል መንጃ ፍቃድ (M) መያዝ ቢፈልጉ፤

- ቢያንስ 18 ዓመት መሙላት አለብዎት
- ህጋዊ የDC የመንጃ ፍቃድ ሊኖርዎት ያስፈልጋል
- የDC የመንጃ ፍቃድ የዕውቀት ፈተናውን ማለፍ ያስፈልጋል።
- የዲሲ የዲ ኤም ቪ የሞተርሳይክል የመንዳት ችሎታዎን የሚያሳዩበትን ፈተና ማለፍ ወይም የሞተር ሳይክል የመንዳት ችሎታዎን የሚያሳዩበትን ትምህርት ተምረው እንደጨረሱ የሚያረጋግጥ የሜሪላንድ ወይም የቨርጂኒያ የምስክር ወረቀት ማቅረብ።

የአገልግሎት ቦታዎች
የዲሲ የዲ ኤም ቪ የሞተርሳይክል የመንዳት ችሎታዎን የሚያሳዩበትን ፈተና ለመፈተን፡ ወደ አንዱ የዲ ኤም ቪ ማእከል መሄድ ይችላሉ። የዲሲ የዲ ኤም ቪ የሞተርሳይክል የመንዳት ችሎታዎን የሚያሳዩበትን ፈተና የሚፈተኑ ከሆነ የሞተርሳይክል የእውቀት ፈተናውን ካለፉ በኋላ የዲሲን የሞተር ሳይክል ለርነር ፐርሚት መያዝ ይኖርብዎታል።

ኤም ዲ ወይም ቪ ኤ ሞተርሳይክል ኦፍ ኮምሊሽን ለማቅረብ ከፈለጉ ወደ ብሬንትዉድ ሮድ ቴስት ፋሲሊቲ በመሄድ በዲሲ የመንጃ ፍቃድዎ ላይ የሞተርሳይክል መንጃ ፍቃድ(M) ማግኘት ይችላሉ።
የሞተርሳይክል ችሎታዎን የሚያሳዩበትን ፈተና ለመፈተን ቀጠሮ ለመያዝ ከፈልጉ በ ኦን ላይን ቀጠሮ መያዝ ወይም በስልክ ቁጥር (202) 727-5000 መደወል ይችላሉ።

Rev. 07/2007

የሞተር ሳይክል መመሪያ

መግቢያ

ሞተርሳይክልን በደህንነት በትራፊክ ፍሰት ውስጥ ለማሽከርከር ልዩ ችሎታና ዕውቀት ያስፈልጋል። የሞተርሳይክል ሴፍቲ ፋውንዴሽን(ኤም.ኤስ ኤፍ) ይህን መማሪያ ሲያቀርብ የሞተርሳይክል ተማሪዎችን የአደጋ የመፍጠርን ሁኔታ ለመቀነስ ነው። መማሪያው አስፈላጊና በድህንነት ለማሽከርከር የሚረዱ መመሪያዎችን የሚያስተምር እንዲሁም ለፍቃድ መስጠት አገልገሎት ስራ እንዲረዳ ሆኖ ነው የተዘጋጀው። ለተማሪው የተዘጋጀ ቢሆንም ሁሉም ሞተርሳይክሊስቶች ከዚህ መማሪያ መጠቀም ይችላሉ።

ኦሪጅናሉ ሞተር ሳይክል ኦፕሬተር ማኑዋል የተዘጋጀው በናሽናል ፓብሊክ ሰርቪስስ ሪስርች ኢንስቲቲዩት (ኤን ፒ ኤስ አር አይ) ሲሆን በናሽናል ሀይዌይ ትራፊክ ሴፍቲ አድሚንስትሬሽን (ኤን ኤች ቲ ኤስ ኤ) ኮንትራት ስር ነው የተዘጋጀው። ከዚህ በተጨማሪ በኤን ኤች ቲ ኤስ ኤ እና ኤም.ኤስ ኤፍ የጋራ ስምምነቶች የሚደረግ ነው። መማሪያውና ተዛማጅ ፈተናዎቹ ለበርካታ ዓመቶች ለተሻሻለው የሞተርሳይክል የመንጃ ፍቃድ መመሪያዎች ሆነው በካሊፎርኒያ ዲፓርትመንት ኦፍ ሞተር ቬክልስ በኤንኤች ቲ ኤስ ኤ ስር በመሆን አገልግልዋል ።

የዚህ መማሪያ አላማ አንባቢው በደህንነት በሚነዳበት ወቅት አደጋ አንዳይደርስበት ለመርዳት ነው። ለዚህ እትም ኤም.ኤስ ኤፍ የኦሪጂናሉን መማሪያ አሻሽሎና አስፍቶ አቅርቦታል።

ይህ ክለሳ ትምህርት የሚያንጸባረቀው፡

- ስለሞተርሳይክል የድህንነት ማሽከርከር ምርምራ የቅርብ ጊዜ ግኝት
- የሞተርሳይክል አሽከካሪዎች፡ የመንጃፍቃድ እንዲሁም የትራፊክ ደህነት ኮሚኒቲዎች ያቀረብዋቸው ሃሳቦች እና መምሪያዎች
- ስለ አልኮሆልና ድራግ የሰፋ ግንዛቤ

የተሻለ የፈቃድ አሰጣጥ ለማዳበር ኤም.ኤስ ኤፍ ከስቴት የፈቃድ ወኪሎች ጋር በቅርበት ይስራል። ይህ ፋውንዴሽን ከግማሽ በላይ የአገራቱንቱን ስቴቶች ሞተር ሳይክል ኦፕሬተር ማኑዋልን ለፍቃድ የመስጠቱ ሂደት እንዲጠቀሙ ረድቷል። የተሻለ የፈቃድ ከከፍተኛ የሞተር ሳይክል አነዳድ ትምህርት ጋር አንዲሁም ከላቀ የህዝቡ ንቃት ጋር ተደማምሮ አደጋ ሊቀንስ ይችላል። የስቴት፣ የግል አንዲሁም የመንግስት ወኪሎችን የሞተርሳይክልን ደህንነት ለመርዳት አባሎች በፋውንዴሽኑ ይገኛሉ።

ቲም ቡቼ
የሞተርሳይክል ሴፍቲ ፋውንዴሽን
ፕሬዚደንት

MSF
MOTORCYCLE SAFETY FOUNDATION®
2 Jenner Street, Suite 150
Irvine, CA 92618-3806
www.msf-usa.org

ለማሽከርከር መዘጋጀት

ተገቢውን የማሽከርከሪያ ልብስ መልበስ.... 4
ሄልመት (የራስ ቁር)አጠቃቀም 4
ሄልመት (የራስ ቁር) አመራረጥ 4
አይንና ፊትን መከላከል 5
አለባበስ.....6
ሞተር ሳይክልዎን ይወቁ 6
ለርስዎ የሚስማማዎት ሞተር ሳይክል 6
መዋስና ማዋስ.....7
የሞተር ሳይክልዎን መቆጣጠሪያዎችን ማወቅ.....7
ሞተር ሳይክልዎን ይቆጣጠሩ.....8
ሀላፊነቶችዎን ይውቁ.....9

ባልዎት ችሎታ ያሽከርክሩ

መሰረታዊው የተሽከርካሪ ቁጥጥር 10
የሰውነት አቀማመጥ 10
ጊርስርን መቀየር 10
ብሬኪንግ 11
ማዞር 11
ርቀትዎን መጠበቅ.....12
የሌይን አቀማመጥ 12
ሌላ ተሽከርካሪን መከተል 13
ማስከተል 14
ማለፍና መታለፍ.....14
ሌይንን መጋራት.....16
የሚቀላቀሉ መኪኖች 16
በጎንዎ ያሉ መኪኖች.....16
ይመልከቱ.....17
መገናኛዎች.....18
ብላይንድ ኢንተርሴክሽንስ.....19
የቆሙ መኪኖችን ማለፍ.....20
መንገድ ዳር ማቆም 20
ጥንቃቄ መጨመር.....21
አለባበስ 21
የፊት መብራት 21
ምልክቶች.....21
የብሬክ መብራት 22
መስተዋትዎን ይጠቀሙ.....22
በራስ የሚደረግ ቁጥጥር.....23
ጡሩምባ 23
በጨለማ መንዳት 24
አደጋን ማስወገድ 24
ፈጥኖ አቅጣጫን መቀየር 24
መወላወል ወይ በፍጥነት መጠምዘዝ ...25
ኮርነሪንግ 26
አደገኛ የመንገዶችን ላይ ማለፍ 27
ምቹ ያልሆኑ መንገዶችና እንቅፋቶች 27
የሚያንሸራትት መንገድ 28
የባቡር ሀዲድ የትሮሊ ሀዲድን የፔቭመንት መክለያዎች(ሲምስ) 29
ግሮቭስ እና ግሬቲንግስ.....29
የሜካኒካል ችግሮች 30
የጎማ መበላሸት.....30
ስታክ ትሮትል.....30
መወላወዝ.....30
የሰንሰለት ችግሮች 31
የኤንጅን መቆም.....31
እንሰሶች 31
የሚበሩ ነገሮች 32
ከመንገድ መውጣት.....32
ተሳፋሪዎችና ጭነት መሸከም 32
እቃዎች.....32
ተሳፋሪዎችን መመሪያ መስጠት.....33
ከተሳፋሪዎች ጋር አብሮ ማሽከርከር 33
ሽክም መሸክም.....33
በቡድን መጓዝ 34
ቡድንን አሳንሶ መጓዝ 34
ከቡድኑ ጋር በአንድነት መቆየት 34
ርቀትዎን መጠበቅ.....34

ለማሽከርከር የሚመች የተስተካከለ ቅርጽ ይህ እውቀት ለምን

አስፈለገ ለማሽከርከር የተስተካለ /ቅርጽ .. 36
አልኮሆልና እና ሌሎች እጾች በሞተር ሳይክል መንዳት ላይ ያለው ተጽእኖ 36
አልኮሆል በሰውነት ውስጥ.....37
የደምውስጥ የአልኮሆል መጠን 37
አልኮሆል እና ሀጉ.....38
ክስና የሚከትሉት ሁኔታዎች.....38
አደጋዎችን መቀንስ.....38
ጓደኞችዎን ወደ መከላከሉ ይሽጋገሩ.....39
ድካም 39

መንጃ ፍቃድዎን ማግኘት

የእውቀት ፈተና 40
የሞተርሳይክል ላይ የችሎታ ፈተና.....41

ለማሽከርከር መዘጋጀት

ረጅም ጉዞ ከመጀመርዎ በፊትና ወደ መድርሻዎም በሰላም እንዲሚደርሱ እርግጠኛ ካልሆኑ ምን ማድረግ ያስፈልግዎታል? ለደህንነቱ የሚጠነቀቅ አሽከርካሪ ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ማስተዋል ያለበት፡

1. **ተገቢውን የማሽከርከሪያ ልብስ መልበስ።**
2. **ሞተር ሳይክሉን ማወቅ ።**
3. **የሞተር ሳይክሉን እቃዎች መመርመር።**
4. **ሀላፊነት የሚሰማው አሽከርካሪ መሆን ይኖርበታል። ተገቢውን የማሽከርከሪያ ልብስ መልበስ**

ተገቢውን የማሽከርከሪ ልብስ መልበስ

በሚነዱበት ወቀት የመንጃ ልብስዎ "ትክክለኛ" የሚሆነው የሚከላከልልዎ ከሆነ ነው።በሆነ የአደጋ ወቅት አራስዎን ለመከላከል እጅግ የተሻለ እድል የሚኖርዎት እኒዚህን ከለበሱ ነው።

- **አስተማማኝ (ሄልሜት)የራስ መከላከያ ቁር**
- **የፊት ወይም አይን መከላከያ**
- **መከላከያ ልብስ**

የሄልሜት (ራስ ቁር) አጠቃቀም

አደጋዎች ሊከሰቱ ይችላሉ፤ በተለይ ባልሰለጠኑ አዲስ ነጂዎች ላይ። ከአምስቱ አንዱ አደጋ የሚደርሰው በጭንቀላት ወይም በአንገት ላይ ነው። የጭንቀላት አደጋ አንደአንገት አደጋ ሃይለኛ ነው ፤ በጣምም የተለመደ ነው። የአደጋ ጥናት አንደሚያመለክተው የጭንቀላት እና የአንገት አደጋዎች አብዛኞቹ ሞተርሳይክል አሽከርካሪዎች ላይ ሃይለኛ ጉዳትና ሞት የሚያስከትሉ ናቸው። ጥናት እንደሚያሳየውም ከጥቂቶቹ በስተቀር የጭንቀላት እና የአንገት አደጋዎች ተገቢውን የራስ መከላከያ ቁር በመልበስ መቀነስ ይቻላል።

አንዳንድ አሽከርካሪዎች የጎን እይታን ይቀንሳል ብለው ስለሚያስቡ የራስ መከላከያ ቁር አይለብሱም። ሌሎችቹምለረጅም ርቀት ወይም በከፍተኛ ፍጥነት ላይ ከሆኑ ብቻ የራስ መከላከያ ቁር ይለብሳሉ። ማጤን የሚኖርብን ሃቆች ፣

- **ተገቢ የራስ መከላከያ ቁር** ወደ ተፈለገው ጎኖች ርቀት ማየት ያስችላል። ከ900 በላይ በደረሱት የሞተርሳይክል አደጎች ላይ በተደረገው ጥናት 40% አሽከርካሪዎች የራስ መከላከያ ቁር የለበሱ ሲሆን በአንዱም ላይ ቢሆን
የራስ መከላከያ ቁር የአደጋን አይታን የሸፈኑበት ጊዜ አልነበረም
- **አብዛኞቹ አደጋዎች የሚደርሱት**

በአጭር የጉዝ ወቀት (ከ5 ማይልስ ያነሰ ርቀት) ማለት ጉዞ በጀመሩ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ነው።

- **አብዛኞቹ አሽከርካሪዎች አደጋ** በሚደርስበት ወቅት ከ30 ማይልስ በሰዓት ያነሰ ርቀት ይጓዛሉ። በዚህ ፍጥነት የራስ መከላከያ ቁር መልበስ የራስ ላይ አደጋውን ቁጥርን ሀይለኝነት በግማሽ ይቀንሰዋል።

የፍጥነቱ ሁኔታ ግምት ውስጥ ሳይገባ የራስ መከላከያ ቁር የለበሱት ካለለበሱት በሶስት እጥፍ ከአደጋው የመትረፍ እድል አላቸው።

የራስ መከላከያ አመራረጥ

ሁለት ዓይነት ተቀዳሚ የራስ መከላከያ ቁር አሉ፤ ሁለት ዓይነትም የተለያየ ሽፋን አላቸው። የፊታችን ሶስት አራተኛና በሙሉ ፊታችንን የሚሸፍኑ።

የፈለጉትን ዓይነት ቢመርጡም ከፍተኛውን የመከላከል ጥቅም እንዲያገኙ የራስ መከላከያው ማሟላት ያለበት የሚከተሉትን ነው።

ራስ ቁር(ሄልሜት)



- **የዲፓርትመንት ኦፍ ስቴትን መስፈርቶች(ዲኦቲ) ያሟላ።** የስኔል ሜሞሪያል ፋዉንዴሽን ምልክት ያለባቸው የራስ ቁሮች (ሄልሜቶች) እንደ ተጨማሪ የአስተማማኝነት ማረጋገጫ ናቸው።
- **ለራስ የሚበቃ ፡** በራሳችን ዙሪያ የሚመቸንና የሚበቃን መሆን አለበት
- **የሚታይ ችግሮች የሌለበት** ይህም እንደ መሰንጠቅ፡ የላላ አስተሳሰር ወይም የተዳከመ ማሰሪያ የመሳሰሉትን ማለት ነው። ማናቸውም የራስ ቁሮች (ሄልሜቶች) ቢመርጡ በሚያሽከረክሩበት ወቅት በራስዎ ላይ በአስተማማኝ ሁኔታ ማሰር። ይህ ካልሆነና አደጋ ካጋጠምዎት ከመከላከሉ በፊት ከጭንቅላትዎ አምልጦ ሊሄድ ይችላል።

አይንና ፊትን መከላከል

የፕላስቲክ የፊት መከላከያ (ይህም መሰባበርን የሚከላከል) ፊትዎን በሙሉ ከአደጋ ለመከላከል ይረዳል። ከንፋስም ፣ከአቧራ፣ ከቆሻሻ፣ ከዝናብ፣ ከነፍሳት እንዲሁም ከፊትዎ ካለው መኪና ከሚስፈነጠር ጠጠር ይከላከልልዎታል። እነዚህ ችግሮች ሀሳብዎትን የሚሰርቁና አሰቃቂ ናቸው። ከነዚህ ችግሮች ጋር የሚጋፈጡ ከሆነ ሙሉ ሀሳብዎትን ወደ መንገዱ ማድረግ የለብዎትዎም።

የአይን መከላከያ (ጎግልስ)እንደ የፊት መከላከያ(ፌስ ሺልድ) የተቀረውን ፊትዎንን ባይከልከላከልልዎትም ይከላከልልዎታል። የንፋስ መከላከያ(ዊንድ ሺልድ) የፊት መከላከያን(ፌስ ሺልድ) ወይም የአይን መከላከያን (ግጎልስ) አይተካም። አብዛኛዎቹ የንፋስ መከላከያ(ዊንድ ሺልድ) አይንዎን ከንፋስ አይከላከልም። እንዲሁም የአይንና የጸሀይ መነጽርም ከንፋስ አይከላከሉም። መነጽሮችም አይንዎን ውሀ ፈሳሽ ከማመንጨት አያድናቸውም፤ በሚነዱበትና ራስዎን በሚያዞሩበት ወቅትም ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ።

ውጤታማ ለመሆን የአይን ወይም የፊት መከላከያ መሆን ያለበት፣

- ከመላላጥ **ነጻ መሆን አለባቸው**
- ከውጭ ለሚመጣ ሰርጎ ገብነት **የመከላከል አቅም ሊኖራቸው ይገባል።**
- ወደ ሁለቱም ጎኖች **በደንብ የሚያሳይ**
- **በአስተማማኝ ሁኔታ የታሰረ መሆን አለበት።** ይህም ተሽቀንጥሮ አንዳይሄድ ይረዳል።
- **አየር የሚያስገባ እንዲሆን ያስፈልጋል።** ጭጋጋማነትን ለማስወገድ አንዲያስችል።
- ለአይን ወይም ለጸሀይ መነጽር ለመጠቅም **በቂ ቦታ ለመስጠት የሚያስችል፤** ቲንትድ አይ ፕሮትቴሽን በማታ ወይም በዝቅተኛ ብርሀን አይለበስም።

አለባበስ

ትክክለኛ አለባበስ በግጭት ወቅት ከአደጋ ይከላከላል፤ ምቾትም አለው። እንዲሁም ከሙቀት፣ ከብርድ፣ ከነገሮች ቅሪት እና ከሚንቀሳቀስቀሱት የሞተር ሳይክሉ ክፍሎች ይከላከላል።

- **ጃኬትን ሱሪዎች** ክንድንና እግርን በሙሉ መሸፈን ይኖርባቸዋል። በነፋስ እንዳይወዛወዙ በሚስያስችል ሁኔታ ከገላችን ጋር በምቹ ሁኔታ ጠብቆ መለበስ ይኖርበታል። ነገርግን እንደፈለጉ ለመንቀሳቀስ በሚያስችል ሁኔታ መሆን አለበት። ይህንን ሁኔታ ለመከላከል የቆዳ ልብስ ተመራጭ ነው። በጥንካሬ የተፈበርኩ ልብሶችም ሊከላከሉልን ይችላሉ። በሞቃታማ አየር ሁኔታም ጃኬት መልበስ ዲሃይድሬሽንን(የውሀ ከሰውነት መትነን) ለመከላከል ይረዳል። አብዛኞቹ ሲፈበረኩ ከልክ ያለፈ ሙቀትን ለመከላከል እንዲረዱ ሆነው ነው የሚመረቱት፤ በክረምት(በሳመር) **ቀናትም ጭምር።**
- **ቡት ወይም ጫማ** ከፍ ያሉና ጠንካራና፣ ቁርጭምጭሚትን ለመሸፈን የሚያስችሉንና ጠንካራ መሆን ይኖርባቸዋል። ሶሎቹ ከጠንካራ፣ ለረጅም ጊዜ ሊቆዩ በሚያስችሉ እንዲሁም መንሸራተትን ለመከላከል በሚያስችሉ ነገሮች መሰራት ይኖርባቸዋል። ሽካራ ነገሮች እንዳይይዝ የጫማው ተረከዝ አጭር መሆን አለበት። የጫማ ማሰሪያ ወደ ውስጥ መከተት ይኖርባቸዋል። ይህም ማሰሪዎቹ በሞተርሳይክሉ እንዳይያዙ ይረዳል።
- **ጓንት** በደንብ ለመያዝና በአደጋ ወቅት አጆችን ለመከላከል ይረዳል። የሚለብሱት ጓንት ከቆዳ ወይም ከተመሳሳይ ለረጅም ጊዜ ሊቆዩ በሚያስችሉ ነገር መሰራት **አለበት።**

በብርድ ወይም በእርጥበት የአየር ሁኔታ ልብሶዎች ሙቀቱን የጠበቀና የደረቀ መሆን አለበት። ከአደጋ መከላከል የሚያስችል መሆን ይኖርበታል። ደንዛዛ ከሆኑ ሞተር ሳይክልን ለመቆጣጠር አይችሉም። በቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ካሽከረከሩ ቅዝቃዜ እና ድካም ሊሰማዎት ይችላል። የዊንተር ጃኬት ነፋስ የሚቋቋምና እስከአንገት፣ የአጅ ስዓት ማሰሪያ ድረስ አንዲሁም ወገብ ድረስ ጥብቅ ብሎ በምቾት ሊለበስ የሚችል መሆን አለበት። ሞተር ሳይክልን ለመንዳት እንዲስማሙ ሆነው የተመረቱ የዝናብ ልብሶች አሽከርካሪዎች በክፍተኛ ፍጥነት በሚጓዙበት ወቅት የመነፋፋትን ወይም የመቀደድን ሁኔታን ይቋቋማሉ።

ሞተር ሳይክልዎን ይወቁ

በሃይዌይ ላይ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ ብዙ ነገሮች **አሉ።** ሞተርሳይክልዎ ከነዚህ ውስጥ አንዱ መሆን የለበትም።
ሞተርሳክልዎት ችግር ውስጥ እንዳይከትዎት፡

- በመጀመሪያ የንብረቱን የባለቤቱን ማኑዋል (መማሪያ) **ያንብቡ።**
- ለራስዎ በሚስማማዎት ሞተርሳይክል ይጀምሩ።
- የሞተርሳይክልዎን **መቆጣጠሪያ** ይወቁ።
- ከማሽከርከርዎ በፊት ሞተርሳይክልዎን **ይቆጣጠሩ።**
- አሽከርክረው እንደጨረሱ ለሚቀጥለው ጊዜ አስተማማኝ አድርገው **ያቆዩ።**
- ሞተርሳይክልዎን ለመንዳት የሚያስችግርዎትን ተቀጥላዎችናና ማሻሽሎችን **ያስወግዱ።**

ለርስዎ የሚስማማዎት ሞተርሳይክል

በመጀመሪያ ሞተር ሳይክልዎ ለርስዎ የሚስማማዎት መሆኑ ያረጋግጡ። **የሚበቃዎት** መሆን አለበት። በሞተርሳይክል ላይ በሚቀመጡበት ወቅት አግርዎ መሬት መንካት ይኖርበታል።

1	*እራስዎን ይፈትኑ*

መሰባበርን የሚቋቋም የፕላስቲክ የፊት መከላከያ፡
ሀ የንፋስ መከላከያ ካልዎት አስፈላጊነት የለውም።
ለ. ዓይንዎን ብቻ ነው የሚከላከልልዎት.
ሐ. ፊትዎን በሙሉ ለመከላከል ይረዳል።
መመ. ፊትዎን አይከላከልም እንዲሁም ጎግሎች ጭምር።

መልስ ገጽ

ቢያንስ የጎዳና ላይ ሞተርሳይክልዎት ሊኖሩት የሚገባው፡

- **የፊት መብራት፣የኋላ መብራት እና የማቆሚያ መብራት**
- **የፊትና የኋላ ማቆሚያ መብራት**
- **የማዞሪያ ምልክት ማሳያ**
- **ጡሩምባ**
- **ሁለት መስተዋቶች**

መዋስና ማዋስ

ሞተርሳይክል በሚዋሱና በሚያውሱ ወቀት ማወቅ ያለብን አደጋው በጀማሪዎች ላይ በብዛት

በተለይ መንዳት በጀመሩ በመጀመርያው ወር ላይ ይበዛል። የማያውቁትን ሞተርሳይክል መንዳት ችግሩን ያብሰዋል። ሞተርሳይክል ከተዋሱ በኋላ ወደ ትራፊኩ ፍሰት ከመግባትዎ በፊት በመጀመሪያ በሚቆጣጠሩት ቦታ ላይ ሆነው በሚገባ ሞተርሳይክልዎን ይወቁት።

ሞተርሳይክልዎን ካዋሱ ደግሞ የሚያውሱዋቸው ሰዎች (ጓደኞችዎ) መንጃ ፈቃድ እንዳላቸውና ማሽከርከር እንደሚችሉ ማረጋገጥ ያስፈልግዎታል።

ምንም እንኳን የማሽከርከር ልምድ ቢኖርዎትም የሚያሽከርክሩትን ሞተርሳይክል አዲስ ወይም የማያውቁት ከሆነ በተጨማሪ ጥንቃቄ ይንዱ ። ከደረሱት አጠቃላይ አደጋዎች ከግማሽ በላይ የደረሱ ከስደስት ወር ላነሰ ጊዜ በሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች ላይ የደረሱ ናቸው።

የሞተር ሳይክል መቆጣጠሪያዎችን ማወቅ

ወደ ጎዳና ላይ ሞተርሳይክልዎን ከማሽከርከርዎ በፊት መቆጣጠሪያዎችን በሚገባ እንደሚያውቁ አረጋግጠው ማወቀ አለብዎት። በንብረቱ ባለቤት የተዘጋጀውን መማሪያ (ማኑዋል) ይውቁ። ይህ በተለይ አስፈላጊነቱ የሚነዱት ሞተር ሳይክል የውሰት ከሆነ ነው።

የማያውቁትን ሞተር ሳይክል የሚነዱ ከሆነ

የሞተርሳይክል መቆጣጠሪያ



- **ሁሉንም ቁጥጥር** በራስዎ ሞተር ሳይክል ላይ **ያከናውኑ።**
- **ሁሉም ነገር የት እንድሚገኝ ይወቁ።** የማዞሪያው ምልክት፣ ጡሩምባ የፊት መብራት ስዊች፣ የነዳጅ መስጫ ቫልቭ፣ ኢንጅን ማቋረጫ ስዊች። በፍለጋ ሳይሆን የት እንደሚገኙ አውቀው ይጠቀሙባቸው ።
- **የጊሩን አጠቃቀም ይወቁ።** በስሮትል ፣በክላች እና በብሬክ ከማሽከርከርዎ በፊት ይጠቅሙና ይውቁት ሁሉም መቆጣጠሪያ የሚያሳየው ውጤት በትንሹም ቢሆን ለውጥ አለው።
- **በጥንቃቄ ያሽከርክሩ።** እንዲሁም አካባቢዎን ይውቁ ፣በቀስታ ፍጥነትዎን ይጨምሩ፣ሲዞሩም ባነስ ፍጥነት ይሁን እንዲሁም ሲያቆሙ ተጨማሪ ቦታ የማቆሚያ ጉዞ ይኑርዎት።
- **ሞተርሳይክልዎን ይቆጣጠሩ**

ለሞተርሳይክል ከመኪና የበለጠ አትኩሮት ያስፈልጋል። የመኪና ትንሽ የቴክኒካዊ ብልሽት አንዳንዴ

ለአሽከርካሪው ያልተመቸ ሁኔታ ከመፍጠር ያላለፈ ችግር ይፈጥራል።

ሞተርሳይክልዎ ችግር ቢኖረው ወደጎዳና ገብተው ማሽከርከርዎ በፊት እንዲያውቁት ያስፈጋል። በእያንዳንዱ ጉዞዎ ወደ ትራፊኩ ፍስት ከመግባትዎ በፊት አጠቃላይ ቁጥጥር ያድርጉ።

ሞተር ሳይክል ላይ ከመውጣትዎ በፊት የሚከተሉትን ቁጥጥር ያድርጉ:

- **ጎማዎች** – የአየር ግፊት፣ መሬት ላይ የሚሽከረከረውን ጎማ አስተማማኝነቱን ይቆጣጠሩ ።
- **ፈሳሾች** –የዘይትና የፈሳሽ መጠንብትንሹም ቢሆን በሳምንት አንድ ጊዜ የሀይድሮሊክ እና የኩላንት ቁጥጥር ያድርጉ። ከሞተርሳይክሉ በታች በመመልከት የዘይት ወይም የጋዝ ፍሳሽ እንዳለ ማየት ያስፈልጋል።
- **የፊት መብራቶች እና**

የኋላመብራት –ሁለቱንም ይቆጣጠሩ። ስዊቹን በመሞከር የክፍተኛውንና የዝቅተኛውን መብራት ሞክረው ይውቁ።

- **የማዞሪያ ምልክት** – የግራና የቀኝ የማዞሪያ ምልክቶች አብርተው ይመልከቱ። ሁሉም መብራቶች በትክክል አንድሚሰሩ ያረጋግጡ።
- **የብሬክ መብራት**– ሁለቱንም የብሬክ መቆጣጠሪያዎች ይሞክሩና በመጠምዘዝ ወቅት የማቆሚያው መብራት እንደሚበራ አረጋግጠ ማወቅ።

ሞተርሳይክል ላይ ከወጡ በኋላ የሚከተሉትን አሟልተው ይቆጣጠሩ፡

- **ክላች እና ስሮትል** – ያለምንም ችግር እንደሚሰሩ ያረጋግጡ። ስሮትል ይዘው ሲለቁት ወደ ኋላ መሄድ አለበት። ክላች ጥብቅ ያለና ላላ ያለ ስሜት መፍጠር አለበት።
- **መስተዋቶች** – ማጽዳትና ሁለቱም መስተዋቶች እንደሚያሳዩን ማረጋገጥ። መስተዋት እያስተካከሉ በአንድ እጅ መንዳት አስቸጋሪ ነው። መስታወቱን ሲያስተካከሉ ካሉበት ሌይን በኋላዎና ካሉበት ሌይን ቀጥሎ ያለውን ሌላ ሌይን ማየት አስኪችሉ ድረስ መሆን ይኖርበታል። ሲስተካከልም የእጅዎን ወይም የትከሻዎን ጫፍ ማየት ይችላሉ። እጅግ አስፈላጊው ግን በኋላዎ ያለውና ከጎንዎ ያለው ነው።
- **ብሬክስ(መግቻ**)– የፊትና የኋላን የብሬክ ሊቨርስ(መግቻ) በአንድ ጊዜ ይሞክሩ። ሁለቱም ብሬክ እስከመጨረሻው በሚጠቀሙበት ወቅት ጠበቅ አንደሚሉና ሞተር ሳይክሉን እንደሚያቆሙት አረጋግጠን ማወቅ ይኖርብዎታል።
- **ጡሩምባ** – ጡሩምውን ሞክረው እንደሚሰራ ያረጋግጡ።.

ከእያንዳንዱ ጉዞዎ አስቀድመው ከሚያከናውኑት ምርመራ በተጨማሪ የሚከተሉትን እቃዎች በሳምንት ቢያንስ አንድ ጊዜ መመርመርዎን ያረጋግጡ። ተሽከርካሪዎቹን፣ ኬብሎቹን፣ የፋስትነሮቹንና የፈሳሾቹን ልክ።የንብረቱ ባለቤት ማኑዋል(መማሪያ) ተመልክተው

ሃሳቦች ያግኙ።

2	እርስዎን ይፈትኑ

ከአጠቃላይ አደጋዎች ከገማሽ በላዩ የሚከሰቱት ምክኒያት

ሀ. ከ35 ማይልስ በላይ በሆነ ፍጥነት ስለሚንዙ ነው።

ለ. በጨለማ ነው የሚደርሱት።

ሐ. ባረጁ ጎማዎች ምክንያት ነው።

መ.ከስድስት ወር ባነስ ጊዜ በሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች ላይ ነው።

መልሱገጽ40

ሀላፊነትዎን ይወቁ

"አደጋ" የሚያመለክተን በማናቸውም ወገን በሚፈጸም ስህተት ወይም የጥንቃቄ ጉድለት ሳይሆን ባለማወቅ የሚፈጽም ነው። አብዛኛውን ጊዜ በትራፊክ ፍሰት ዋናው ጉዳይ ይህ ባይሆንም በትክክለኛው አብዛኛዎቹ አደጋ ያጋጠማቸው ሰዎች ለደረሰው አደጋ መነሻ የተወሰነ ሃላፊነት ለመሸከም መጠየቅ ይችላሉ።

እንበልና አንድ ሰው በመገናኛ ላይ ቢጫ መብራት ወደ ቀይ በሚቀየርበት ወቅት እንቅስቃሴውን ለማቆም ማቆሚያውን ይይዛል። ያሉበት መንገድ መብራትም ወደ አረንጓዴ ይለወጣል። እርስዎም ዘግይተው ሊመጡ የሚችሉትን ከግምት ሳያስገቡ ወደ መገናኛው ይንቀሳቀሳሉ። በዚህም ሁለታችሁም ወደዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ትገባላችሁ። ማቆም የአሽከርካሪው ሃላፊነት ነበር። እንዲሁም አይቶ ወደ መገናኛው መግባት የርስዎ ሀላፊነት ነበር። ሁለታችሁም የመጨረሻውን አሴፈላጊ ነገር አልፈጸማችሁም። አደጋ ሊያስከትል የሚችለውን የክስተቶቹን ሰንሰለት ሌላኛው ወገን ስለጀመረው ማንኛችንም ከተጠያቂነት ልናመልጥ አንችልም።

እንደአሽከርካሪ መጠን ሌሎች አሽከርካሪዎች ያዩኛል ወይም የማለፍ መብት ይሰጡኛል ብሎ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። አደጋ የመድረሱን እድል ለመቀነስ :

- **የሚታዩ ይሁኑ** ፡ ተስማሚውን ልብስ ይልበሱ። የፊት መብራትዎን ይጠቀሙ። ይበልጥ ማየትና መታየት በሚችሉበት ሌይን ላይ ሆነው ያሽከርክሩ።
- **ሀሳብዎት ያስተላልፉ**፡ ተገቢውን ምልክት፣ የብሬክ መብራት እንዲሁም የሌይን ላይ አቀማመጥ ይጠቀሙ።
- **አደጋን ለመከላከል የሚያስችል በቂ ቦታ ይተዉ**፡ ሲከተሉ፣ ሌላው ወገን ሲከተልዎት፣ ሌይን ሲጋሩ፣ ሲያልፉ ወይም ሲታለፉ
- **የ12 ሰከንድ ርቀት ባለው ሁኔታ አልፈው መንገድዎን** እያስተዋሉ ይጓዙ።
- **ብዛት ያላቸውን አደጋዎች** ያስተውሉ እንዲሁም ለይተው ይወቁዋቸው።
- **ደርጊት ለመፈጽም ዝግጁ ይሁኑ** ፡ ንቁ ሆነው ይቆዩና አደጋ ሊያስወግዱ የሚያስችሉ ተገቢ ዘዴዎችን ይወቁ።

በአደጋ ምክኒያት አንድ ሰው ከተጎዳ በኋላ ውንጀላ ምንም አያመጣም። የአንድ ወገን የአደጋ መነሻ በጣም ጥቂት ጊዜ ነው የሚያጋጥመው። ንቁ ሆነው የመንዳት **ችሎታዎ ፣ ወሳኝ የሆኑ** ውሳኔዎችን ወስነው የመተግበር ሁኔታዎ ክልሎች ሁሉም ይልቅ ተጠያቂዎችን ለመለየት ይረዳል።

ያስታውሱ። በሆነ የአደጋ ወቅት የአደጋ ምክኒያት ላለመሆን ወይም ካልተዘጋጁበት የአደጋ ተጠያቂነት ነጻ ለመሆን ውሳኙ እራስዎ **ነዎት**።

ባልዎት ችሎታ ያሽከርክሩ

ይህ ማኑዋል(መማሪያ)እንዴት አቅጣጫ፣ ፍጥነት ወይም ሚዛንን እንዴት እንደሚቆጣጠሩ ሊያስተምርዎት አይችልም። ይህን ከልምድ ብቻ ነው ሊማሩ የሚችሉት። ነገር ግን መቆጣጠሩን ማውቅ የሚጀምሩት ችሎታዎን አውቀውና የመንገድ ላይ ህጎችን ታዘው ሲሄዱ ነው።

መሰረታዊ የተሽከርካሪ ቁጥጥር

የሰውነት አቀማመጥ

ሞተርሳይክልን በጥሩ ሁኔታ ለመቆጣጠር

- **ቅርጽ**፡ ሲቀመጡ እጆችዎ ሞተርን ለማስነሳት እንጂ እራስዎን ለመደገፍ መሆን የለበትም።
- **መቀመጥ**፡ ሲቀመጡና እጆታዎችን ሲይዙ ከእጅታዎቹ ጋር ያልዎት ርቀት ክንድዎን በትንሹ ብቻ የሚታጠፍ ብቻ መሆን አለበት። እጅዎን በትንሹ ማጠፍ በሞተርሳይክሉ መያዣ ላይ ያሉትን ሳይንጠራሩ ለመጫን ያስችልዎታል።
- **እጆች**

  እጆችዎ ሀንድልግሪፕስን አጥብቀው ሲይዙ ሽካራውን መሬት ቆንጥጠው ለመያዝ ይረዳዎታል። ሲጀምሩም እጅዎን ዘርግተው ይጀምሩ። ይህም ከመጠን በላይ ስሮትል

የእጆታ አያያዝ



እንዳይጠቀሙ ይረዳዎታል። በተጨማሪ እጆታውን እንደሚያመቹ አድርጎ መያዝ እጅዎ ከክርኖችዎ ወይም ከክርኖችዎ በታች አንደሚሰሩ ሆነው **በማስተካከል ጡንቻዎች** በልኩ ሞተርሳይክልዎን ለመምራት ያስችልዎታል።

- **አብራኩ** ሞተርሳይክልዎን በሚያዞሩበት ወቅት አብራክዎትን ከነዳጅ ማከማቻው በተቃራኒ መሆናቸው ሚዛንዎን ለመጠበቅ ይረዳዎታል።
- **እግሮች**– እግርችዎን በእግር ማሳረፊያዎቹ ላይ ማድረግ ሚዛንዎን ለመጠበቅ ይረዳዎታል።እግሮችዎን አይጎትቱ። እግሮችዎ በሆነ ነገር ቢያዝ ሊጎዱና ሞተርሳይክልዎ መቆጣጠር ሊያስችግርዎት ይችላል። እግርዎትን ከመቆጣጠርያው አጠገብ ያድርጉ። **ይህም በተፈለገበት ወቅት በፍጥነት ለማግኘት ይረዳል። የእግርዎ ጣቶች ወደመሬት ማመልከት የለባቸውም። በመንገዱና በእግር ማሳረፊያዎቹ መካከል ሊያዙ ይችላሉና።**

ጊርስ መቀየር

የፈለጉትን አይነት ፍጥነት ለመምረጥ ጊርስ በቀላሉ ከመቀያየር በላይ አይጠየቁም። የማርሽ አጠቃቀም ወደ ታች ሲወርዱ፣ ሲያዞሩ ወይም በከፍታዎች ላይ ሲያስነሱ መማር ለአስተማማኝ የሞተርሳይክል እንቅስቃሴ አስፈላጊ ነው።

ከክላቹ ጋር ጊርሶቹን ወደ ታች በማድረግ **ፍጥነት መቀነስ** ወይም ማቆም ይቻላል። በሚቆሙበት ወቅት በመጀመሪያ ጊር ላይ አደርገው ያቆዩት። ይህም መንቀሳቀስ ሲፈልጉ ቶሎ እንዲነሱ ይረዳዎታል።

በዝቅተኛ ጊር ላይ በሚያሽከረክሩበት ወቅት በዝቀተኛ ፍጥነት እንደሚጓዙ እርግጠኛ ይሁኑ። ይህን ካላደረጉ ሞተር ሳይክሉ በመንቀጥቀጥ የኋላው ጎማ ሊንሸራተት ይችላል። ወደ ቁልቁል በሚጓዙበት ወቅት ወይም ወደ መጀመሪያ ጊር በሚቀይሩበት ወቅት ብሬክ ተጠቅመው ፍጥነት መቀነስ ያስፈልግዎታል። ክላቹን ለቅቅ በማድረግ ምቹ የሆነ ሁኔታ መፍጠር በተለይ ወደ ዝቅተኛ ፍጥነት በሚቀይሩበት ወቅት ያስፈልግዎታል።

ወደ ማዞርያ ከመግባትዎ በፊት ጊርስ መቀየር በጣም ጥሩ ነው።ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በሚያዞሩበት ወቅት መቀየር አስፈላጊ ነው። ይህን ካደርጉ ማስታወስ ያለብዎት ፍጥነትዎትን ከቀነሱ በዝግታ ማድረግ ያስፈልግዎታል። ድንገተኛ የሀይል ለውጥ የኋላ ተሽከርካሪውን ሊያንሸራትተው ይችላል።

ብሬኪንግ

ሞተርሳይክልዎ ሁለት ብሬክስ አሉት። አንድ የፊትና አንድ የኋላ። ሁለቱንም በአንድ ወቅት ይጠቀሙ። ከፊት ያለው ፍሬን በጣም ሀይለኛ ሲሆን **ቢያንስ** የማቆሚያውን **ሃይል ሰጭ አራተኛውን** ያህል ይሸፍናል ። ከፊት ያለው ብሬክ አስተማማኝነት የሚኖረው በአግባብ ከተጠቀመበት ነው።

ያስታውሱ:

- ፍጥነት መቀነስ ወይም ማቆም ከፈለጉ ሁልጊዜ **ሁለቱንም ብሬክስ በአንድ ላይ ይጠቀሙባቸው**። በተለመደ የማቆም ሁኔታም ቢሆን ሁለቱንም ብሬክስ በአንድ ላይ መጠቀም ለአስቸጋሪና አስቸኳይ ሁኔታ ጥሩ የማቆም ልማድ ለማዳበር ይረዳል። የፊቱን ብሬክ ይዘው እንዲሁም የኋላውን ወደታች ይጫኑት። የፊቱን ብሬክ ጨብጠው ከያዙት ወይም የኋላውን በሀይል ወደ ታች ከተጫኑት የብሬክ መቆለፍ ብሎም የመቆጣጠር ችግር ሊያስከትል ይችላል።
- **ቴክኒኩን ካውቁ** ሁለቱንም ብሬክስ በአንድ ላይ መጠቀም ይቻላል ። ቢሆንም በከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ሞተር ሳይክሉ ወደ ጎን ዘንበል በሚልበት ወቅት ከመሬት ጋር ያለው የተወሰነ መነካካት ከመሬቱ ጋር ኮርነሪንግ(ማእዘን) ለመስራት ያገልግላል። ከዚህ አነስ ያለ መነካከት በማቆም ወቅት ይኖራል።ብዙ ብሬክ ከተጠቀሙ መንሸራተት ሊከሰት ይችላል።

የፊት ፍሬን በሚያንሸራትት መሬት ላይ ያለአግብብ መጠቀም አደገኛ ነው። በጥንቃቄ የሊቨር ብሬክን **እምቅ አድርገው ይያዙ**። ነገርግን ጨብጠው አይያዙት

- **አንዳንድ ሞተር** ሳይክሎች የተቀናጀ ብሬኪንግ ሲስተምስ አላቸው።ይህም የኋላ ብሬኪንግ ፔዳል ሲጠቀሙ የፊትና የኋላ ብሬክስን በአንድ ላይ ያቀናጃቸዋል። (የንብረት ባለቤቱን ማኑዋል(መምሪያ) በመመልከት ስለአጠቃቀሙና ስለውጤታማ እጠቃቀሙ ዝርዝር ማብራሪያውን ይመልከቱ)

ማዞር

አሽከርካሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ኩርባ ላይ ወይም በማዞር ወቅት በጣም ይፈጥናሉ። ማዞሩን መቆጣጠር ሲያቅታቸውም ወደ ሌላ ሰው የትራፊክ ፍሰት ሌይን ይገባሉ ወይም ከመንገድ ውጪ ይሆናሉ። ወይም ከአቅም በላይ ይሆንባቸውና በሀይል ብሬክ በመያዝ የመንሸራተት እና ከቁጥጥር ውጪ የመሆን ሁኔታ ይከተላል።

ማዞርንና ኩርባን በጥንቃቄ ማለፍ ያስፈልጋል።.

ለተሻለ ቁጥጥር 4 ደረጃዎችን ይከተሉ

- **ፍጥነት ይቀንሱ**
- **ይመልከቱ**
- **ይጫኑ**
- **ያሽከርክሩ**
- **ፍጥነት ይቀንሱ**፡ ከማዞርዎ በፊት ስሮትሉን በመዝጋት ፍጥነት ይቀንሱ። አስፈላጊ ከሆነም ሁለቱንም ብሬኮች ይጠቀሙ።
- **ይመልከቱ** ፡ ማዞር ወደ ፈለጉበት ይመልከቱ። ትከሻዎን ሳይሆን ራስዎን አዙረው እንዲሁም የማየትዎ ልክ ግን እይታዎ አካባቢ መመልከት መቻል አለበት።
- **ይጫኑ** ፡ ለማዞር ሞተር ሳይክሉ ዘንበል ማለት አለበት። ሞተርሳይክሉን ወደ ጎን ዘንበል ለማድረግ መያዣውን ማዞር ወደሚፈልገበት አቅጣጫ ይጫኑት ወደ ግራ ይጫኑ ፡ ወደ ግራ ዘንበል ይበሉ፡ ወደ ግራ ይሂዱ። ወደ ቀኝ ይጫኑ ፡ ወደ ቀኝ ዘንበል ይበሉና ወደ ቀኝ ይሂዱ። በከፍተኛ ፍጥነት እና(ወይም) በጠባብ የማዞር ሁኔታ ሞተርሳይክሉን ይበልጥ ወደ ጎን እንዲያዘነብል ማድረግ ያስፈልግዎታል።

- **ያሽከርክሩ** – በሚያዞሩበት ወቅት ስትሮትሉን በማዞር ሊከሰት የሚችለውን ያለተረጋጋ እንቅስቃሴ ማረጋጋት ይችላል። በሚያዞሩበት ወቅት በአንድ ዓይነት ፍጥነት ወይም ቀስ በቀስ ፍጥነትዎን በመጨመር ይዙሩ። ይህም ሞተር ሳይክልዎን ለማረጋጋት ይረዳል። በተለመደ የማዞር ወቅት አሽከርካሪውና ሞተርሳይክሉ በአንድ ላይና በተመሳሳይ ማእዘን ወደ ጎን ዘንበል ይላሉ።

የተለመደ ማዞር

በቀስታና በጠባቡ በሚያዞሩበት ወቅት ሞተርሳይክልዎን ወደ ጎን ዘንበል በማድረግ ሰውነትዎን ቀጥ አድርገው ሚዛንዎን ጠብቀው መንዝ ይችላሉ።

በዝግታ፣ በጠባቡ መጠምዘዣ

3 እረስዎን ይፈትኑ

በሚያሽከረክሩበት ወቅት:

ሀ. ፊትዎንና ትከሻዎን በመጠምዘዝ ወደ ሚዞሩበት ይመልከቱ።

ለ. ክንድዎ ቀጥ ያለ ይሁን።

ሐ. አብራክዎን ከጋዝ ታንክ ወዲያ ያድርጉት።

መ. ራስዎንና ዓይንዎን ወደ ሚሄዱበት አቅጣጫ ያዙሩት።

መልስ -ገጽ 40

ርቀትዎን መጠበቅ

የበለጠው ራስን የመጠበቅ መንገድ ርቀት መጠበቅ ነው። "አደጋ ለማስወገድ የሚያስችል ቦታ" በሞተር ሳይክልዎ አካባቢ **ማድረግ ነው**። ይህም አንድ ሰው ቢሳሳት በርስዎና በተሳሳተው ሰው መካከል ያለው ርቀት:

- **እርምጃ ለመውሰድ ጊዜ ይኖርዎታል።**
- **ለመንቀሳቀስ ጊዜ ይኖርዎታል።**

የሌይን አቀማመጥ

አንዳንድ ጊዜ የሞተር ሳይክልዎ መጠን ሊጠቅምዎት ይችላል። በማብራሪያው ላይ **እንደተመለከተው እያንዳንዱ** የትራፊክ ፍሰት ያለው ሌይን ሞተር ሳይክልን ሶስት የጉዞ መንገድ አሉት። *የሚሄዱበት ሌይን አቀማመጥ :*

- **የማየትና የመታየት ችሎታዎን** ይጨምርልዎታል
- የሌሎችን ንቁጠ **ግርዶሽ ያስወግዳል።**
- የመንገድ ላይ አደጋዎችን **ያስወግዳል**
- ያሉበትን ሌይን በሌሎች አሽከርካሪዎች እንዳይያዝ **ይከላከልልዎታል።**
- የሚፈልጉትን ነገር **እንዲያስተላልፉ** ይረዳል
- ከሌሎች በፍጥነት ከሚመጡ ተሽከርካሪዎች የሚመጣውን የንፋስ ሀይል **ያስወግድልዎታል።**
- የማምለጫ መንገድ **ይሰጥዎታል።**

ተስማሚውን መንገድ በመምረጥ አደጋን ለማስወገድ የሚያስችለውን የቦታ ክፍተት በመጨመር በሌሎች ይታዩ።

የሌይን አቀማመጥ



በአጠቃላይ ለአሽከርካሪዎች በሞተርሳይክል ዙሪያ አንድ የበለጠና ቦታና አደጋን ለማስወገድ የሚያስችል የክፍተት ቦታ የለም። የሌይኑ ማናቸውም ቦታ መተው የለበትም። መሀሉም ቢሆን።

እራስዎን በሌሎች በሚታዩበትና ሊከስት ከሚያስችል አደጋ እንዳይደርስ ከሚያስችልዎት ርቀት ላይ ይሁኑ። የትራፊኩ ሁኔታ ሲቀይር እርስዎም ቦታ ይቀይሩ። አሽከርካሪዎችና ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች በግራዎ ብቻ የሚገኙ ከሆነ በመንገድ ቁጥር 2 ወይም ቁጥር 3 ላይ ያሽከርክሩ። ችግሮች በቀኝዎ ብቻ የሚገኙ ከሆነ በመንገድ ቁጥር 1 ወይም ቁጥር 2 ላይ ይቆዩ። ተሽከርካሪዎች በግራና በቀኝዎ የሚሄዱ ከሆነ መካከለኛውን ሌይን ማለትም መንገድ ቁጥር 2 ን ተመራጭ ያድርጉ።

በመካከለኛ ክፍል ያለው ከመኪናዎች ላይ የሚንጠባጠበውን የሚያከማችው አይል ስትሪፕ(መተላለፊያ) አብዛኛውን ጊዜ ከሁለት ፊት በላይ ስፋት የለውም። መንገዱ አርጥብ ካልሆነ በስተቀር የተለመደው መካከለኛ ስትሪፕ በደህንነት ለመንዳት ከመሬት ጋር ያለው ትራክሽን(መሬቱን ቆንጥጦ የመያዝ ሁኔታ) አስተማማኝ ነው። ከመተላለፊያው (ግሪስ ስትሪፕ) ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ፍቀቅ ብለው እያሽከረከሩ በትራፊኩ ሌይን መካከለኛ ቦታ ላይ ማሽከርከር ይችላሉ። የትራፊክ ፍሰት በበዛበት መገናኛ መንገድ ወይም በቶል ቡዝ ላይ የሚገኝ ትልቅ የኦይል እና የግሪስ ክምችት ላይ አያሽከርክሩ።

ማስከተል

"በጣም በቅርብ ርቀት መከተል" የሞተርሳይክል አሽከርካሪዎችን ለአደጋ ከሚዳርጉት ምክኒያቶች አንዱ ሊሆን ይችላል። በትራፊክ ፍሰት ሞተርሳይክሎች ልክ እንደመኪናዎች ለማቆም የሚሄዱት የማቆሚያ የመንገድ ጉዞ ያስፈልጋቸዋል።

በተለምዶ ከፊት ለፊታ ካለው ተሽከርካሪ ጋር በትንሹ በሁለት ደቂቃ የገዝ ልዩነት ወደ ኋላ መሆን ያስፈልጋል።

የሚከተሉበትን ርቀት ለማወቅ ፡

- **ለምልክት የሚሆን ቦታ ይምረጡ።** ይህም ያሉበት ወይም ከፊት ለፊትዎ ያለው የእግረኛ መንገድ ምልክት ወይም የመንገድ መብራት ቋሚ ሊሆን ይችላል።.
- **ከፊት ለፊትዎ ያለው የተሽከርካሪ የኋላ የመከላከያ (ባምፐር)** ምልክቱን እንዳለፈ ሰከንዶችን ይቁጠሩ፡ " አንድ ሺ-አንድ፣ አንድ ሺ-ሁለት"
- "ሁለት" ብለው ከመቁጠርዎ በፊት ወደ **ምልክቱ ቢደርሱ** በጣም በቅርብ ርቀት እየተከተሉ ነው።.

ከፊት ለፊትዎ ያለው አሽከርካሪ በድንገት ቢያቆም የሁለት ደቂቃ የመከተል ጊዜ ለመቆም ወይም ለመንቀሳቀስ የመዘጋጃት ጊዜ ይሰጣል። በመንገዱ ላይ ያሉትን አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉትን የተበላሹ ቦታዎችንና ያሉትን ሌሎች አደጋዎች በተሻለ ሁኔታ ያሳያል።

ሞተር ሳይክልዎ ከተለምዶው ረዘም ባለ ቦታ የሚያቆም ከሆነ ተልቅ ያለ አደጋን ለማስወገድ የሚረዳ የመጠበቂያ ርቀት ቦታ ያስፈልገዋል ። መንገዱ የሚያንሸራትት ከሆነ፣ ከመኪና ውስጥ ሆነው ወደፊት ማየት ካልቻሉ፣ ወይም የትራፊክ ፍሰቱ ብዙ ከሆነ፣ ወይም አንዱ ከፊትለፊትዎ ቢያቆም የሶስት ደቂቃ የመከተል ርቀት ይክፈቱ።



ለመቆም ቢገደዱም ከተሽከርካሪው በኋላ ሆነው መከተሉን በጥሩ ሁኔታ ያድርጉት። ይህም አንድ ሰው ከወደኋላ ወደርስዎ ቢጠጋ በቀላሉ ለማምለጥ ያስችልዎታል። ከፊትዎ ያለውም ተሽከርካሪ በሆነ ምክኒያት ወደ ኋላ መምጣት ከጀመረ ሊከሰት ከሚችለው አደጋ የማምለጫ ቦታ ያገኛሉ።

ከመኪና በኋላ ሲሄዱ አሽከርካሪው የኋላ መመልከቻ መስተዋት ማየት በሚችልበት ቦታ ይሁኑ። በሌይኑ የመካከለኛ ቦታ ላይ ሲሆኑ በኋላ መመልከቻ መስተዋት መሀል ምስልዎን ማየት አለብዎት። ሹፌሩም ሊያይዎትም የሚችልበት ቦታ ነው።

ራቅ ባለ በሌይኑ ጎን ቢያሽከረክሩ አሽከርካሪው በጎን መስተዋት ሊያይዎት ይችላል። ነገር ግን ማስታወስ ያለብዎት አሽከርካሪዎች የኋላ መመልከቻ መስተዋት የሚያዩትን ያህል የጎን መስተዋትን በብዛት **አይመለከቱም**። የትራፊክ ፍሰቱ ሁኔታ ቢፈቅድልዎት የሌይኑ የመካከለኛ ቦታ አብዛኛውን ጊዜ ለርስዎ የበለጠውና ለእርስዎ ከፊት ለፊት ያሉት አሽከርካሪዎች እንዲታዩ የሚያስችልዎት ቦታ ሲሆን ሌይኑን ሌሎች እንዳይጋርዎት ይከላከልልዎታል።

ተሽከርካሪ ሲከተልዎ

ከኋላዎ የሚከተልዎትን ለመለየት ፈልገው ፍጥነትዎን ቢጨምሩ መጨረሻው በከፍተኛ ፍጥነት የሚደረግ መከተል ይሆናል።

የኋላ ተከታይን ለመላቀቅ የተሻለው መንገድ ከፊት ለፊትዎ እንዲሆን ማመቻቸት ነው። አንድ ሰው ወደርስዎ ቢጠጋ ሌይኖች ቀይረው ያሳልፉት። ይህን ማድረግ ካልቻሉ ፍጥነትዎን ቀንሰው ከፊትዎ ባለው ስፍራ ለርስዎና ለተከታይዎ ለማቆም የሚያስችል በቂ ተጨማሪ ስፍራ ክፍት ያድርጉ። በዚህም ተከታዮችዎ ለማለፍ ይበረታታሉ። ተከታዮችዎ ካላለፉም ለራስዎና ለተከታዮችዎ በቂ ስፍራን ስለተው ከፊት ለፊትዎ አዋጣሪ ሁኔታ ቢመጣ እንኳን እርምጃ ለመውሰድ ይችላሉ።

ማለፍና መታለፍ

ማለፍና መታለፍ ከመኪናው ሁኔታ ብዙ የተለየ አይደለም። ነገርግን እይታ ይበልጥ ይፈልጋል። ሌሎች ሽከርካሪዎች እንደሚያዩዎት ያረጋግጡ። ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ይመልከቱ።

ማለፍ

1. የበለጠ እንዲያዩና እንድታዩ በአስተማማኝ የመከተል ርቀት በሌይኑ **በግራ በኩል ይንዱ። ምልክት** ያሳዩ እንዲሁም ከፊት ለፊት የሚመጣውን የትራፊክ ፍሰት ይቆጣጠሩ። መስትዋትዎን ተጠቅመው እንዲሁ ዞረው ከበስተኋላዎ ይመልከቱ።
2. የተመቸ ሁኔታ ሲያገኙ ወደግራ ሌይን ይንቀሳቀሱና ፍጥነት ይጨምሩ። የሚያልፉትን መኪና የማያጨናንቅና አደጋ ለማስወገድ የሚያስችል ስፍራ የሚሰጥ የሌይን አያያዝ ይምረጡ።
3. **በንቁጠ ግርዶሽ ላይ** በተቻልዎት ፍጥነት **ይንዱ**.
4. ወደ መጀመሪያው ሌይን ከመመልስዎ በፊት **እንደገና ምልክት ያሳዩና** የመስትዋትና በራስዎ የሚደረገውን መቆጣጠር ይጨርሱና ምልክት ማሳያውን ያጥፉት።

ያስታውሱ።ማለፍ በሚፈቀድበትና በተመልከተ የፍጥነት ልከ መፈጽም ያስፈልጋል። ምልክቶችንና የመንገድ ላይ ምልክቶችን ይውቁ።

መታለፍ

ከኋላዎ ወይም ከፊትዎ በሚመጣ መኪና በሚታለፉበት ወቅት ባሉበት ሌይን መካከለኛ ቦታ ላይ ይሁኑ። ወደእነርሱ ቀረብ ብለው የሚያሽከረክሩ ከሆነ ለአደገኛ ሁኔታ ሊዳርግዎት ይችላል።

ሊያስወገዱዋቸው የሚገቡ ግጭቶች

- **ሌላ ተሽከርካሪ**፡ በርስዎ ወይም በሚያልፈው ተሽከርካሪ የሚፈጽም ትንሽ ስህተት የጎን ፍትጊያ ልያስከትል ይችላል።
- **ተቀጥላ መሰትዋቶች** ፡ አንዳንድ አሽከርካሪዎች መስተዋታቸው ከመከለከያቸው ያለፈ መሆኑን ይረሱታል።
- **ከመስኮት የሚውረወር ነገሮች**፡ አሽከርካሪው ቢያይዎትም ተሳፋሪው ላያይዎትና የሆነ ነገር ወደርስዎ ወይም ከፊትዎ ወዳለው መንገድ ሊወረውር ይችላል።
- ከትላልቅ መኪናዎች የሚመጣ የንፋስ ግርፋት፡ የመቆጣጠር ችሎታዎን ሊያስችግረዎት ይችላል። መሀል ቦታዎ ላይ ሆነው በንፋሱ ግርፋት ከተመቱ ስህተት የመፈጽምዎ ሁኔታ በጎኖቹ ላይ ከሚሆኑ ይልቅ ከፍያለ ነው።

የሚያልፍዎት መኪና ካለበት የሌይኑ ክፍል ወደ ራቀ ቦታ **አይንቀሳቀሱ**። ይህ ሁኔታ ሌላ ተሽከርካሪን ወደ ሌይንዎ በመጋበዝ በቶሎ በመግባት ሊያቋረጥዎ ይችላል።

ማለፍ



መታለፍ



ሌይን መጋራት

መኪኖችና ሞተርሳይክሎች በደህንነት ለማሽከርከር ሙሉ ሌይን ያስፈልጋችዋል። ሌይን መጋራት አብዛኛውን ጊዜ ክልክል ነው።

በቆሙ ወይም በሚንቀሳቀሱ የመኪናዎች ረድፍ መካከል ባልጠበቁት ሁኔታ ወደ አደጋ ሊመራዎት ይችላል። ከመስኮት እጅ ሊወጣብዎት ይችላል፣ በር ሊከፈት ይችላል፣ መኪና በድንገት ሊጠመዘዝም ይችላል። የሌሎችን ሌይን የመጋራት አካሄድ አያበረታቱ። አሽከርካሪዎች ወደ አሉበት አቅጣጫ በመጠጋት የማቆም ሙከራ ሲያደርጉ የመንገዱን መካከለኛ ቦታ በመያዝ ይቆዩ። አሽከርካሪዎች ይህን የማድረግ ሁኔታ ይስባቸዋል።

- **በከባድ** የመኪናና የመኪና ባምፐር(መከላከያ)በሚጠጋጉበት የትራፍክ ፍሰት ሁኔታ።
- **ሊያልፉዎት** በሚፈልጉበት ወቅት።
- መገናኛ ላይ ለማዞር **በሚዘጋጁበት** ወቅት።
- ወደ ኤግዚት በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ወይም ሀይ ዌይን **በሚለቁበት** ወቅት።



የሚቀላቀሉ መኪናዎች።

አሽከርካሪዎች በራምፕ መግቢያ ላይ ሆነው እርስዎ ሀይዌይ ላይ እንዳሉ ላያይዎት ይችላሉ። በቂ ስፍራ ይስጡ። ክፍት ሌይን ካገኙ ወደ ሌይኑ ይሸጋገሩ። ክፍት ካልሆነም ፍጥነትዎን በመጨመር በቂና ወደ ሀይዌዩ ለመቀላቀል የሚያስችላችውን ክፍተት ይተዉላችው።

በጎንዎ ያለ መኪና

የግድ ካልሆነብዎት በጎንዎ ከሚገኝ መኪና ወይም ትራክ አጠገብ አያሽከርክሩ። በሚቀጥለው ሌይን ባለው የንቁጠ ግርዶሽ እይታ ሊጋረዱና ያለማስጠንቀቂያም ወደ ሌይንዎ ሊገባብዎት ይችላል። በሚቀጥለው ሌይን ላይ ያሉት መኪናዎችም ባሉበት ሌይን አደጋ ቢያጋጥምዎት እንዳያመልጡ ሊጋርድዎት ይችላሉ። ፍጥነት በመጨመር ወይም ፍጥነት በማቀዝቀዝ ከትራፊክ ፍሰት ነጻ የሆነ ቦታ በሁለቱም ጎንዎችዎ ያግኙ።



4 እራስዎን ይፈትኑ

ከኋላዎ በቅርበት የሚከተልዎትን ለመቆጣጠር፡ :

ሀ. ሌይኖች በመቀየር ያሳልፍዋቸው።

ለ. ጡሩምባ በማስማት እንዲሁም አጽያፉ አካላዊ ምልክቶች ያሳዩ።

ሐ. በርስዎና በቅርብ ርቀት በሚከታተልዎት መካክል ያለውን ፍጥነት ይጨምሩ።

መ. ከግምት አያስገቧቸው።

መልሱገጽ - 40

ይመልከቱ

ጥሩ ልምድ ያላቸው አሽከርካሪዎች በአካባቢያቸው ስላለው ነገር እውቀት አላቸው። የመንዳት ስልታቸውን ሲ በሚባለው ባለሶስት ደረጃ መንገድ በመጠቀም ተገቢ ፍርድ ለመስጠት፣ በተለያየ የትራፊክ ፍሰት ሁኔታዎች ላይ ለመተግበር ያስችላቸዋል።

- ሰርች(መፈለግ)
- ኢቫሉዌይት(መገምገም)
- ኤክሰኪዩት(መፈጸም)

እነዚህን ደረጃዎች እንመርምራቸው።

ሰርች(መፈለግ)

በሀይል ወደ ፊት ፍለጋውን ይቀጥሉ። ወደ ጎንዎና ወደኋላ በመፈለግ ሊከሰቱ የሚችሉትን አደጋዎች ያስወግዱዋቸው። ከመፈጸማቸው በፊትም ቢሆን። ምን ያህል ጊዜና ቦታ እንዳልዎት በዝርዝር ቢፈልጉ አደጋ ለማስወገድና ለመቀነስ ይረዳዎታል። ለማምለጫ የሚያስችልዎትን ቦታ በመገናኛ ላይ ወይም አካባቢ በመፈለግ ፣ በመገበያያ ቦታዎች ትምህርት ቤትና የግንባታ ክልሎች ላይ ያተኩሩ።

የሚከተሉትንም ይፈልጉ:

- **ወደርስዎ የሚመጣን** የትራፊክ ፍሰት፤ ከፊትዎ ወደግራ ሊጠመዘዝ የሚችል።
- ከግራና ቀኝ የሚመጣ **የትራፊክ ፍሰት**
- ከኋላ የሚመጣን **ትራፊክ**
- **አደገኛ** የመንገድ ሁኔታዎች

በተለይ የተወሰነ እይታ ባለበት አካባቢ ንቁ ይሁኑ። ብዙ የሚታይ ነገር ባለበት አካባቢ እርስዎንና ሞተርሳይክልዎን በሌሎች ከመታየት ሊሸፍንዎት ይችላል።

ኢቫሉዌይት(መገምገም)

ከአደጋ ጋር ሲጋፈጡ ምን ያህል አስቸጋሪነት እንደሚፈጥርብዎት ያስቡ ሊክስቱ የሚችሉ ችግሮችን ሊገጥምዎት እንደሚችል ይጠባበቁ **እንዲሁም ችግሮቹን ለመቀነስ ያቅዱ።**

- **የመንገድ ወይም የመንገድ ላይ ባህሪያት**፡ የመንገድ ላይ የተቦረቦሩ ክፍተቶች፣ የሀይ ዌይ የመከላከያ አጥሮች፣ ድልድዮች፣ የቴሌፎን ቋሚዎች እና ዛፎች ወዳሉበት ባይመጡም የማሽከርከር ሁኔታዎን ሊያሰናሉት **ይችላሉ።**
- **የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች** ፡ ወደ የትራፊክ ምልክት መስጫዎችን፣ የማረጋጊያ ምልክቶችን(ሬጉላቶሪ) ጭምር፣ ማስጠንቀቂያ ምልክቶች፣ እንዲሁም የመንገድ ላይ ምልክቶች ከፊት ለፊትዎ ያሉትን ሁኔታዎች ለመገምገም ያስችልዎታል።
- **አሽከርካሪዎች እና ሌሎች ትራፊክ** ፡ ወዳሉበት ሊመጡና አደጋ የመከሰቱን ሁኔታ ሊጨምር ይችላል።

ደህንንትዎን ለመጠበቅ የሚያስችልዎትን ሰዓትና ቦታ ያሰላስሉ። አዋጣሪ ሁኔታ ከመጣብዎት ግብረመልስ ለመስጠት የሚንቀሳቀሱበትን ጊዜ ያስቡ።

ኤክሰኪዩት(መፈጸም)

ውሳኔዎን ይተግብሩ።

የበለጠ ቦታ ለመፍጠርና ጉዳት ለመቀነስ

- በመብራትና(ወይም) ጡሩምባ **መኖርዎን ያሳውቁ**
- ፍጥነትዎን በመጨመር፣ በማቆም በመቀነስ **ያስተካክሉ።**
- አቀማመጥዎንና/ወይም አቅጣጫዎን **ያስተካክሉ።**.

የጥንቱን “ አንድ ነገር በአንድ ጊዜ” የሚለውን አባባል ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አደጋዎች ለማስተናገድ ይጠቀሙ። ሁለት አደጋዎች ካጋጠሙዎት ፍጥነትን ተጠቅመው አደጋዎቹን ይለያዩዋቸው።ከዚያም አንድ በአንድ መፍትሄ ይፈልጉላቸው። ሶስት ወይም ከዚያ በላይ አድጋዎች ሲጋጥሞት ውሳኔ መወሰን ይበልጥ ይከብዳል። ሊመጣ የሚችለውን ይመዝኑና ለአደጋዎቹ እኩል ርቀት ይስጡ።

ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉትን እንደመገናኛ የመገበያያ ስፍራዎች፣ ትምህርት ቤቶችና የኮንስትራክሽን ቀጠናዎች ላይ ክላቹንና ሁለቱንም ብሬኩን በመጠቀም እርምጃ ለመውሰድ የሚችሉበትን ጊዜ ይቀንሱ።

5	እራስዎን ይፈትኑ

እርምጃ ለመውሰድ የሚያስፈልግዎን ግዜ ለመቀነስ ማድረግ ያለብዎ:

ሀ. ከፍጥነቱ ልክ ባነሰ ያሽከርክሩ ለ ክላቹንና ብሬኩን ይሸፍኑ

ሐ. ፍጥነት ሲቀንሱ ወደ ኒውትራል ይለውጡ

መ. በሚዞሩበት ጊዜ ክላቹን ይሳቡት

መልስ ገጽ-40

መገናኛዎች

በርስዎና በሌሎች የትራፊክ ፍሰት መካከል ለሚያጋጥም ግጭት ዋናው ቦታ መገናኛ ነው። መገናኛ በአርባን ኤሪያ መሀል ወይም በመኖሪያ ቤቶች መንገድ ድራይቭ ዌይ ሊሆን ይችላል፤ ማንኛቸውም የትራፊክ መንገድ ያሉበትን መንገድ ሊያቋርጥዎ ይችላል። ከሚያጋጥሙት የሞተርሳይክል(መኪና) ግጭቶች የሚከሰቱ በአሽከርካሪው የመንጃ ተራ በመግባት ነው። ከፊትዎ የሚመጡና በቀኝዎ በኩል ወደ ግራ የሚዞሩ መኪናዎችና ከጎንዎ ወዳሉበት ሌይን የሚገቡ መኪናዎች ትላልቆቹ አደጋዎች ናቸው። በመገናኛዎች ላይ የርስዎ የሲ አጠቃቀም(ገጽ 17) ወሳኝ ነው።

ሌሎቹ እንደሚያዩዎት ምንም ማረጋገጫ የለም። “ የዓይን ግንኙነትን” ሹፌሩ የመሄድ የባለተራ መብት እንደሰጥዎት ምልክት አድርገው አያስቡ።በጣም ብዙ ጊዜ አሽከርካሪ ወደ በትክክል ወደ ሞተርሳይክሉ ቢመልከትም “ሊያየው(ያት)” ግን ይሳነዋል። መተማመን ያለብዎት በራስዎት አይን መሆን አለበት። መኪና ወደ መንገድዎ ቢገባብዎት መኪናው ያደርገዋል ብለው ያስቡ። ጥሩ አሽከርካሪዎች ምን አደጋ ይኖራል ብለው ከመግባት ይቆጠባሉ።

ዘው ብለው አይገቡም። በመገናኛ ላይ የመታየት እድልዎን ይጨምሩ። የፊትዎ መብራት ተጠቅመው በሌይኑ ላይ ከፊትዎ ወደርስዎ የሚመጣውን ትራፊክ እይታ የበለጠ እንደሚያሳይዎት አስተውለው ያሽከርክሩ። አደጋ ለማምለጥ የሚያስችል ቦታ በመያዝ በሞተር ሳይክሉ ዙሪያ ይተዉ።

ትንንሽ መገናኛዎች



ትላልቅ መገናኛዎች



ወደ መገናኛው በሚቀርቡበት ወቅት አሽከርካሪው ይበልጥ በሚያይዎት የሌይኑ ቦታ ላይ ይሁኑ። ክላቹንና ሁለቱንም ብሬኮች በመጠቀም እርምጃ ለመውሰድ የሚጠቀሙበትን ጊዜ ይቀንስልዎታል።

ወደ መገናኛው በሚቀርቡበት ወቅት ፍጥነትዎን ይቀንሱ። ወደ መገናኛው ከገቡ በኋላ ለመዞር ከሚዘጋጁ መኪኖች ይራቁ። በመሰረቱ ፍጥነትዎን ወይም አቀማመጥዎን አይቀይሩ። አሽከርካሪው/ዋ ለመዞር የሚዘጋጁ ነው የሚመስለው/ላት።

ብላይንድ ኢንተርሴክሽንስ

ብላይንድ ኢንተርሴክሽን በሚቃረቡበት ወቅት በተቻለዎት መጠን ሊታይ ወደሚችሉበት በመጀመሪያው ጊዜ ወደ ሌላ የማሽከርከሪያ ቦታ ይንቀሳቀሱ። በስዕሉ ላይ እንደተመለከተው አሽከርካሪው ወደ ሌይኑ የግራ ቦታ ተንቀሳቅስዋል፤ ከቆመው መኪና አለፍ ብሎ ማለት ነው፤ ይህም ከመንገድ አልፎ ያለው ተሽከርካሪ በተቻለ ፍጥነት እንዲያየው ይረዳል።

ብላይንድ ኢንተርሴክሽንስ



ያስታውሱ። በተቻለ መጠን ማየት ያለብዎት ሲሆን ቦታዎን እየሸፈኑ በሌሎች እንድሚታዩም ያረጋግጡ።

የማቆም ምልክቶች



የማቆም ምልክት ወይም የማቆም መስመር ላይ ቢደርሱ እዛው ያቁሙ። ትንሽም ሄድ ብለውም እንደገና ይቁሙ፤ የሚያቋርጥዎ ሌይንና ሌይንዎ የሚገናኝበት ላይ ይሁኑ። ከዚያም ቦታ ከሰውነትዎ ወደ ፊት ተስበው በአካባቢዎ ወዳሉት ሕንጻዎች፣ የቆሙትን መኪናዎች ወይም አውቶብሶችን በመመልከት የሚመጣውን ነገር ልብ ይበሉ። በሚመልከቱበት ወቅት የፊትዎ ጎማ ከመሻገሪው መስመር እንዳላለፈ ያረጋግጡ።

የቁሙ መኪናዎችን ማለፍ

የቆሙ መኪናዎችን ሲያልፉ ካሉበት ሌይን ወደ ግራ ቦታ ተጠግተው ይለፉ። በር በመክፈት ሊመጣ ከሚችል ችግር፣ በር ከፍተው ከሚወጡ አሽከርካሪዎች ወይም ከመኪናዎች መካከል ከሚወጡ ሰዎች ይጠንቀቁ። ወዳሉበት የሚመጣ የትራፊክ ፍሰት ካለ በሌይኑ መሀል ላይ መቆየት አብዛኛውን ግዜ ተመራጭ ነው። ሌይኑ መሀል መሆን አደጋን ለማስወገድ የሚስችል የመከላከያ የቦታ ክፍተት እንዲኖረዎት ይረዳል።

አሽከርካሪው ከኋላ ያለውን የትራፊክ ፍሰት ሳያረጋግጥ ከከርቡ ቢንቀሳቀስ የከፋ ችግር ያጋጥማል። ቢመለከትም ላያይዎት ይችላል።

6 እራስዎን ይፈትኑ

ከሌሎች አሽከርካሪዎች ጋር የዓይን ግንኙነት ማድረግ:

ሀ. እርስዎን ማይታቸው ጥሩ ምልክት ነው።.
ለ. ከሚጠይቀው ጥረት አኳያ ሲታይ አስፈላጊ አይደለም።

ሐ. አሽከከካሪው እንዲያልፉ ይፍቅድልዎታል ማለት አይደለም።

መ. አሽከርካሪው ማለፍ እንደሚፈቅድልዎት ያረጋግጣል።

መልስ ገጽ- 40

የቆሙ መኪናዎች



በሁለቱም ሁኔታዎች አሽከርካሪ ወዳሉበት መንገድ ሊያቋረጥዎት ይችላል። ቀስ ብለው በመጓዝ ወይም ሌኖች በመቀየር ለሚያቋርጡት ስፍራ በመተው ያመቻቹለት።

በድንገት U-ተርን የሚያረጉት መኪናዎች ከሁሉም የበለጠ አደገኞች ናቸው። በአጠቃላይ ሊያቋርጥዎት፣ በሙሉ መንገድዎን ሊያግድዎትና ያለምንም መሄጃ ቦታ ሊያስቀርዎት ይችላል። አሽከርካሪው ምን ማድረግ እንደሚገባው መንገር ስለማይችሉ ፍጥነትዎን በመቀነስ የአሽከርካሪውን አትኩሮት ያግኙ። ጡሩምባ አሰምተው በጥንቃቄ መንገድዎን ይቀጥሉ።

መንገድ ዳር ማቆም ከከርቡ በ 90°አንግል ያቁሙ። የኋላው ተሽከርካሪም ከርቡን እዲነካው ያድርጉ።

መጠምዘዣ ላይ መኪና ማቆም



ጥንቃቄ መጨመር

ከሞተር ሳይክሎች ጋር በሚደርጉት ግጭቶች አሽከርካሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ሞተር ሳይክሉን አላየነውም ይላሉ። ከፊትም ሆነ ከኋላ ሲታይ የሞተር ሳይክል የውጭ ገጽታ ከመኪና ጋር ሲወዳደር በጣም ትንሽ ነው። ፍለጋ የማያካሄዱበትን ነገር ማየትም ከባድ ነው። አብዛኛዎቹ አሽከርካሪዎችም ፍለጋቸው ወደ ሞተርሳይክል አይደለም። እንዲያውም አደጋ የሚያስከትልን መኪና በሚፈልጉበት ወቅት የሚያዩት በቀጭኑ የሚታየውን የባለሁለት አሽከርካሪውን የውጭ ገጽታውን ነው።

አሽከርካሪው መምጣትዎን ቢያይም ከአደጋ ነጻ ሆነዋል ብሎ መደምደም አይቻልም። ትንንሽ ተሽከርካሪዎች እርቀት ላይ ያሉና ከሚሄዱበት ፍጥነት ባነሰ ፍጥነት የሚሄዱ **መስለው** ይታያሉ። አሽከርካሪዎች ብዙ ግዜ አንዳላቸው አስበው ከሞተር ሳይክል ፊት ሆነው ካሉበት ወጥተው እንደሚሄዱ የተለመደ ነገር ነው። አብዛኛውን ጊዜ ግን ይሄ ስህተት ነው።

ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ እራስዎንና ሞተርሳይክልዎን በሌሎች እንዲታዩ ለማድረግ የሚያስችሉ ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ።

አለባበስ

አብዛኞቹ አደጋዎች የሚደርሱት በቀን ጊዜ ነው። ደመቅ ያሉ ልብሶችን በመልበስ የመታየት እድልዎን ይጨምሩ። ያስታውሱ ከአሽከርካሪው ወይም ከሞተር ሳይክሉ ክፍል በግማሹ የሚታየው ክፍል **ሰውነትዎ ነው**።

ደማቅ ብርትኳንማ፣ ቀይ፣ ቢጫ፣ ወይም አረንጓዴ ጃኬቶች ወይም ቨስትስ ለመታየት የሚያስችልዎት የበለጡት ምርጫዎች ናቸው። የራስ ቁር(ሄልሜት) ከአደጋ ከመከላከል ባሻገር ጥቅም አላቸው። ደማቅ ከለር ያላቸው ራስ ቁሮች(ሄልሜትስ) በሌሎች እንዲታዩ **ይረዳዎታል**።

ማናቸውም ደማቅ ከለር ከተራ ወይም ከጨለማ ከለሮች ይሻላል።አንጸባራቂ፣ ደማቅ ከለር ያለው አለባበስ(የራስ ቁር(ሄልሜት) እና ጃኬት ወይም ቨስት) የበለጡ ምርጫች ናቸው።

በቨስት ላይና በራስ ቁር (ሄልሜት) ጎኖች ላይ ያለ አንጸባራቂ ነገር አሽከርካሪዎች ካሉበት የጎን ስፍራ ወዳሉበት ቦታ እንዳይመጡ ይከላከላከልልዎታል። አንጸባራቂ ነገር ከፊትም ከኋላም ለሚመጡ አሽከርካሪዎች ጥልቅ እገዛ አለው።

የፊት መብራት

በሌሎች አንዲታዩ የበለጠው መንገድ የፊት መብራትዎን አብርተው ማቆየት ነው፤ **በሁሉም ጊዜያት** (ከ1978 ጀምሮ በዩ.ኤስ.ኤ. የተሸጡት ሞተርሳይክሎች እውቶማቲካል በሆነ ሁኔታ መብራታቸው የሚበራው በሚንቀሳቀሱበት ወቅት **ነው**።) **ጥናቶች እንደሚያሳዩን** በቀን ጊዜ መብራት ያበራ ሞተር ሳይክል በሌሎች የመታየቱ ሁኔታ በሁለት እጥፍ ይልቃል። በማታና በጭጋግ ጊዜ የአጭር ጨርሩን መብራት ይጠቀሙ።

ምልክቶች

በሞተር ሳይክል የሚገኙት ምልክቶች በመኪና ላይ ከሚገኙት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ለሌሎች ምን ለማድረግ እንደፈለጉ ይጠቁማሉ።



በሞተርሳይክሉ ተጨማሪ ለአደጋ የመጋለጥ ሁኔታ ምክኒያት ምልክቶች የበለጠ አስፈላጊ ናቸው። ሌይኖች መለወጥ ወይም መዞር በሚፈልጉበት ወቅት ይጠቀሙባቸው። ምንም ሰው የለም ብለው በሚያስብቡት ወቅትም ይጠቀሙባቸው። ከፍተኛውን ችግር የሚያመጣብዎት የማያዩት መኪና ነው ። የምልክት መብራትም ቦታዎን **ለመቀየር ቀላሉ መንገድ ነው።** ለዚህም ነው በሚቀይሩበት ወቅት የማዞር እቅድዎ የታወቅ ቢሆንም ምልክት ማሳየቱ ጥሩ ሃሳብ የሆነው።

ወደ ነጻ መንገድ በሚገቡበት ወቅት ከኋላዎ ያሉት አሽከርካሪዎች ናቸው የምልከትዎን ብልጭ ድርግም ማለት አይተው ቦታ የሚያመቻችልዎት።

ከእያንዳንዱ መዞር በፊት የምልክት መብራትዎን ማሳየት በአካባቢዎ ያለውን የትራፊክ ፍሰት ረብሻና መሸማቀቅ ይቀንሳል። ከዞሩ በኋላም መብራትዎን መብራትዎ መጥፋትዎን ያረጋግጡ።ይህ ካልሆነ አሽከርካሪው እንደገና የሚጠመዘዙ መስሎት ወደ መንገድዎ ይገባል። በእያንዳንዱ የመዞር ወቅት አሽከርካሪዎች ከወዲሁ **እንደየአስፈላጊነቱ እርምጃ መውሰድ እንዲችሉ ምልክት ያሳዩ። ሌሎቹ ማድረግ የፈለጉትን በግምት እንዲያውቁ አይተዋቸው።**

የብሬክ መብራት

የሞተርሳይክልዎ የብሬክ መብራት እንደመኪናው የብሬክ መብራት አብዛኛውን ጊዜ የሚታይ አይደለም፤ በተለይ የኋላው መብራት(ቴልጌይቱ) ሲበራ።(ከፊት መብራቱ ጋር አብሮ ነው የሚሰራው።) ሁኔታው ከፈቀደልዎት ፍጥነትዎን ከመቀነስዎ በፊት የብሬክ መብራትዎን በማብራት ለሌሎቹ ምልክት በማሳየት ይርዷቸው።የብሬክ መብራትዎን ማብራት የሚጠቅመው በተለይ ከታች ከተጠቀሱት አስቸጋሪ ነው።

- ሌሎችይቆማሉ ብለው **ከሚጠብቁበት ፍጥነት በላይ ፈጥነው በሚቆሙበት** ጊዜ(ከከፍተኛ የሀይዌ ፍጥነት ጉዞ በሚዞሩበት ወቅት።)
- ሌሎቹ ፍጥነትዎን ይቀንሳሉ ብለው በማይጠብቁበት ወቅት **ፍጥነትዎን በሚቀንሱበት ጊዜ።** (በብሎክ ወይም በአሌይ ላይ)

በቅርበት ሌሎች የሚከተልዎት ከሆነና ፍጥነትዎን የሚቀንሱ ከሆነ የብሬክ መብራትዎን ፍጥነትዎን ከመቀንስዎ በፊት ያብሩት። ከኋላዎ የሚከተልዎትን ከፊትዎ ያለውንና ፍጥነትዎን የሚያስቀንስዎትን ነገር አያዩትም። ይህ ከኋላ ተጠግቶ የሚከተልዎትን እንዳይጠጋዎትና ከፊት **የተጋርጠውን የማይታያቸው አደጋ እንዳለ ያስጠነቅቃቸዋል።**

መስትዋትዎን ይጠቀሙ

ከፊትዎ ያለን ነገር መከታተሉ ይበልጥ አስፈላጊ ቢሆንም ከኋላዎ ያሉትን ሁኔታዎች መናቅ የለብዎትም። የትራፊክ ሁኔታዎች በፍጥነት ይቀንሳሉ። ከኋላው ያለውን ነገር ማወቅዎ ከፊትዎ ለሚያጋጥሞዎት ችግር አስተማማኝ ውሳኔ ለመውሰድ ይረዳዎታል።

የማያቋረጥ የመስተዋት ቁጥጥር ማድረግ የተለምደ የፍለጋ ዘዴዎ መሆን አለበት። መስታዋትዎን **በአስፈላጊነት የሚጠቀሙት በሚከተሉት ላይ ነው።**

- **በመገናኛ ላይ ሲቆሙ።**ከኋላዎ የሚመጡትን መኪናዎች ያስተውሉ። አሽከርካሪዎቹ በርስዎ ላይ አትኩሮት ካላደረጉ ክመታየትዎ በፊት በላይዎ ላይ ሊሄድብዎት ይችላል።
- **ሌይኖች ከመቀየርዎ በፊት።** ማንም ሊያልፍዎት እንዳልሆነ ያረጋግጡ።
- **ፍጥነትዎን ከመቀነስዎ በፊት** ። ከኋላዎ ያለው አሽከርካሪ ፍጥነትዎን ይቀንሳሉ ብሎ ላይጠብቅ ወይም የት እንደሚቆሙ እርግጠኛ አይሆንም። ለምሳሌ የማዞር ምልክት እንዳሳዩ አሽከርካሪው ራቅ ባለው መገናኛ ላይ የሚዞሩ እንጂ በቅርበት ባለው ድራይቭ ዌይ አይዞሩም ብሎ ያስባል።

መስትዋት መጠቀም



አንዳንድ ሞተር ሳይክሎች ክብ(ኮንቬክስ) መስትዋት አላቸው። ይህም ከዝርጉ መስትዋቶች በበለጠ ሰፋ ያለ ምስል ለማየት ያስችላል። መኪናዎቹንም ካሉበት ይበልጥ የራቁ አስመስሎ ያሳያል። የኮንቬክስ መስትዋቶችን የማያውቋቸው ከሆነ ይወቁዋቸው *(በሚቆሙበት ወቅት በመስትዋትዎ ውስጥ የቆመ* ***መኪና ይምረጡ። በሀሳብዎ ምን ያህል እንደራቀ ያስቡ። ከዚያም ዞረው ምን ያህል*** *እንደቀረቡ ይመልከቱ።)ጥሩ የርቀት አዋቂ እስከሚሆኑ ድረስ በመስትዋትዎ ልምምድዎን ይቀጥሉ። ከዚያ በኋላም ቢሆንም ሌይኖች ከመቀየርዎ በፊት ተጨማሪ ጉዞ ይጓዙ።*

በራስ የሚደረግ ቁጥጥር

መስትዋቶዎን መቆጣጠሩ ብቻ በቂ አይደለም። ሞተርሳይክሎች እንደ መኪና "ንቁጠ ግርዶሽ" አላቸው። ሌይኖች ከመቀየርዎ በፊት ራስዎን አዙረው ወደ ጎንዎ በመዞር ሌሎች መኪኖችን ይመልከቱ።

ብዙ ሌኖች ባሉበት መንገድ ላይ ራቅ ያለውን ሌይንና ካሉበት ሌይን ቀጥሎ ያሉትን ይቆጣጠሩ።

ራቅ ባለው ሌይን ላይ ያለው አሽከርካሪ ሊሄዱ ወዳቀዱት ቦታ ሊያመራ ይችላል።

ተጨማሪ የራስ መቆጣጠር ማድረግ የመንገድ ላይ የተለመደ የፍተሻ ተግባርዎ ይሁን። **በአካባቢዎ** ያለውን ነገር ካወቁ ብቻ ነው ሊገጥሙት የሚችሉት።

ጠራምባ

የአንድን ሰው አትኩሮት በፍጥንነት ለማግኘት ከፈለጉ ጠራምባ ለመጠቀም ዝግጁ ይሁኑ።

ማንምኛውም ወዳሉበት የሚመጣን ሌይን ፈጠን ያለ ጠራምባ ማሰማት ጥሩ ሀሳብ ነው።

ከሚያጋጥሙት ውስጥ የሚከተሉት ናችው፤

- ከጎንዎ ባለው ሌይን ላይ ያለው **አሽከርካሪ** ከፊት ለፊት ካለው ተሽከርካሪ ተጠግቶ ሲያሽከረክርና ለማለፍ ሲፈልግ።
- **በቆመ መኪና** ውስጥ በአሽከርካሪው መቀመጫ ላይ ሰው ካለ።
- **በመንገዱ ላይ ሰው ካለና** ብስክሊት የሚነዳ ከሆነ ወይም የሚራመድ ከሆነ።

በአጣዳፊ ጊዜ ጠራምባውን በረጅም ጎላ አድርገው ያሰሙት። ለማቆም ወይም ከአደጋው ቦታ ለማምለጥ ይዘጋጁ።

ማወቅ ያለብዎት የሞተርሳይክል ጠራምባ የመኪናን ያህል የጎላ ድምጽ የለውም። ስለዚህ **ቢጠቀሙበትም** አይተማመኑበት። ሌሎች ስልቶች በመጠቀም ጠርምባውን መጠቀም ይቻላል።

በማታ መንዳት

በማታ ማየትም ሆነ መታየት ከባድ ነው። ለሌሎች አሽከርካሪዎች የሞተርሳይክልዎን የፊቱን ወይም የኋላውን መብራት ከመኪና መብራቶች መለየት ቀላል አይደለም።

ይህንን ለማካካስም ማድረግ ያለብዎት፡

- **ፍጥነትዎን ይቀንሱ**። በቀን ብርሃን ከሚያሽከረክሩበት ባነሰ ፍጥነት ይጓዙ፤ በተለይ በጥሩ ሁኔታ በማያውቁት መንገድ ላይ። ይህም አደጋ የማስወገዱን እድል ከፍ ያደርግዋል።
- **የሚሄዱትን ርቀት ይጨምሩ**: የጉዞ ርቀትን በምሽት መገመቱ በቀን ከመገመቱ ይቀላል። አይኖችዎ በጥላዎችና በብርሃን ላይ በመመርኮዝ የሚመጣው ነገር ምን ያህል ርቀት እንዳለውና በምን ያህል ፍጥነት እንደሚጓዝ ያውቃሉ። እነዚህ ግምቶች በጨለማ ላይ ሲሆን አንዲሁም በሰው ሰራሽ መብራቶች ላይ የሌሉ ወይም የተሳሳቱ ይሆናሉ። የሶስት ደቂቃ ወይም ከዚያ በላይ የመከተል ርቀት ይኖርዎት። እንዲሁም ለማለፍ እና ለመታለፍ የሚያስችል ተጨማሪ ርቀት ይኑርዎት።.
- **ከፊት ለፊት ያለውን መኪና ይጠቀሙ**፡ ከከፍተኛው የሞተርሳይክልዎ ብርሀን ይበልጥ ከፊትዎ ያለው የመኪና መብራቶች የበለጠ
እይታ ይሰጥዎታል። ከኋላዎ የሚከተልዎ ብርሀን ወደ ላይና ወደታች ማለት ባምፐ ወይም ሻካራ ፔቭመንት እንዳለ ያስጠንቅቅዎታል።.
- **ከፍተኛውን ብርሀን ይጠቀሙ** ፡ ማግኘት የሚቻልዎትን ያህል ብርሃን ሊኖርዎት ይገባል። መኪና በማይከተሉበት ወይም በማያገኙበት ወቅት ከፍተኛውን ብርሃን ይጠቀሙ። በሌሎች እንደሚታዩ ያረጋግጡ፤ በምሽት በሚያሽከረክሩበት ወቅት የሚያንጸባርቁ ነገሮች ይልበሱ።.

7	እራስዎን ይፈትኑ

አንጸባራቂ ልብሶች መሆን ያለባቸው:

ሀ. በምሽት የሚለበሱ ይሁኑ

ለ. በቀንየሚለበሱይሁኑ

ሐ. መለበስየለባቸውም

መ. በቀንና በለሊት ይለበሱ

መልስ - ገጽ 40

አደጋን ማስወገድ

ምንም ያህል ጠንቃቃ ቢሆኑም በጠባብ ቦታ ውስጥ የሚገቡበት ጊዜ አለ። እንደነዚህ አይነት ሁኔታዎችን የማለፍ እድልዎ በሚወስዱት ተገቢ የፍጥነት እርምጃ ይወሰናል። አብዛኛውን ጊዜ አደጋ የሚከሰተው አሽከርካሪው ስላልተዘጋጀ ወይም አደጋን ለማስወገድ የሚደረጉ የእንቅስቃሴዎች ችሎታ ስለሌለው ነው።

አሽከርካሪዎን መቼና እንዴት ማቆም እንዳለብዎት ወይም ፈጥነው አቅጣጫዎን መቀየር እንዳለብዎት ማወቅ አደጋን ለማስወገድ የሚረዱ ሁለት ወሳኝ ችሎታዎች ናቸው። ሁልጊዜ በፍጥነት አቁመው ከአደጋው ማምለጥ ተስማሚ ምርጫ አይሆንም ወይም አይቻልም። አሽከርካሪዎች ከአደጋ ጋር በሚገጥሙበት ጊዜ ፈጥነው አቅጣጫን መቀየርም መቻል አለባቸው። ለሚያጋጥመው ሁኔታ የትኛውን ችሎታ መጠቀም እንደሚያስፈልግ **ማወቁም አስፈላጊ ነው**።

ጥናቶች እንደሚያሳይዩ አብዛኞቹ አደጋ የደርሰባቸው አሽከርካሪዎች:

- የፊቱ ጎማ ላይ **ከተለመደው ባነሰና** የኋላውን ጎማ ላይ እንዲሁም ከተለመደው በላይ ብሬክ ሲጠቀሙ ነው።
- ብሬኪንግንና ፈጥኖ አቅጣጫን ከመቀየር አለመለየት ወይም ፈጥኖ አቅጣጫን መቀየር በሚስፈልግበት ጊዜ አለመጠቀም። ሀሳብ ጥሩ ምክር ይሰጣል።

በፍጥነት ማቆም

በፍጥነት ለማቆም ሁለቱንም ብሬክስ በአንድ ላይ ይጠቀሙባቸው። የፊቱን **ብሬክ ለመያዝ አይፍሩ**። "ጨብጠውም " አይያዙት። የብሬክ ሊቨሩን ጥብቅ አድርገው እንዲሁም ጨመቅ ጨመቅ በማድረግ አንዳስፈላጊነቱ ይጠቀሙ። የፊቱ ተሽከርካሪ መንቀሳቀስ ቢያቆምም የፊት ብሬክስን ውዲያውኑ ይልቀቁትና እንደገና ጠበቅ አድርገው ይጠቀመብት። በዚያን ጊዜ የኋላውን ብሬክ ወደ ታች ይጫኑት። በድንገትም የኋላውን ብሬክ በጥሩ ሁኔታ ቆንጥጠ መያዝ በሚችል መንገድ ላይ የኋላውን ብሬክ ቢቆልፉት አሽከርካሪዎ ፊጽሞ እስከሚቆም ድረስ እንደተቆለፈ ማቆየት ይችላሉ። ነገር ግን በተቆለፈ የኋላ ተሽከርካሪም ቢሆንም ሞተር ሳይክልዎን መቆጣጠር ይችላሉ፤ ነገር ቀጥ ባለ መስመር የሚሄድ ሆኖ ቀጥ ያለ መሆን **አለበት**።

የማቆሚያ ርቀት



ለማቆም ሲፈልጉ **ሁልጊዜ** ሁለቱንም ብሬክስ በአንድ ላይ ይጠቅሙባቸው። የፊቱ ብሬክ 70% ወይም ከዚያ በላይ የማቆም ሀይል አስተዋጾ ያደርጋል።

ከርብ በሚዞሩበት ወይም በሚያሽከርክሩበት ወቅት የግድ ማቆም ካለብዎት የበለጠው ቴክኒክ በመጀመሪያ ሞተርሳክልዎን ቀጥ አድርገው ሲነዱና በመቆየት በመቀጠልም ብሬክ ይጠቀሙ። ቢሆንም ሁልጊዜ ሞተርሳይክልዎን ቀጥ አድርገው ማሽከርከርና ማቆም ላይችሉ ይችላሉ። ዘንበል በሚሉበት ጊዜ የግድ ማቆም ካለብዎት ቀለል ያለ ብሬክ ይጠቀሙ። እንዲሁም ስሮትሉን ይቀንሱ። በሚያቆሙበት ጊዜ ዘንበል የሚሉበትን ማእዘን **መቀነስ** ይችላሉ፤ ተጨማሪ የብሬክስ ግፊት በመስጠት ሞተርሳክልዎ ቀጥ **እስከሚልና** ክፍተኛ የብሬክ ግፊት እስከሚሆን ድረስ ነው። በመጨረሻዎቹ የማቆሚያ የጉዞ መንገድ(ፊትስ) የሀንድልባሮቹን ቀጥ አድርገው መያዝ አለብዎት። ሞተርሳይክሉም "ቀጥ" ማለትና ሚዛኑን መጠበቅ አለበት።

ፈጥኖ አቅጣጫን መቀየር

ሁለቱንም ብሬኮች በተገቢው መንገድ ቢጠቀሙም አንዳንድ ጊዜ ለማቆም የሚበቃ ቦታ ላይኖርዎት ይችላል። በመንገድዎ ላይ የሆነ ነገር በድንገት ሊያጋጥምዎት ይችላል። ወይም ከፊትዎ ያለው መኪና የማቆም ድምጽ ሊያሰማ ይችላል። አደጋን ለማስወገድ ብቸኛው ዘዴ መዞር ወይም ባሉበት በፍጥነት አቅጣጫን መቀየር ነው።

በፍጥነት አቅጣጫን መቀየር ድንገተኛ የአቅጣጫ ለውጥ ነው። በሁለት በኩል የሚደረግ መዞር ወይም በፍጥነት ወደጎን የሚደረግ አንቀስቃሴ ነው። ለማምለጥ ወዳሰቡት ጎን ትንሽ ግፊት በሀንድ ግሪፕ ላይ በመጠቀም ከአደጋው ማምለጥ ይቻላል። ይህም ሞተርሳይክሉ በፍጥነት ጋደል እንዲል ይረዳል። መዞሩ ከጠበበ ጋደል የማለቱ ሁኔታም ይጨምራል።

ከሰውነትዎ ቀጥ ብለውና በሚዞሩበት አቅጣጫም ጋደል ብለው እንዲሁም አብራክዎ ከነዳጅ ታንኩና በተቃራኒ አቅጣጫ ላይ ሲሆን እንዲሁም እግርዎን በእግር ማስቀምጫው ላይ በማድረግ ነው።

ይንሸራተቱ፣ ከዚያ ፍሬን ይያዙ



ያቁሙ ከዚያም አቅጣጫ በቶሎ



ሞተርሳይክሉ በርስዎ ቁጥጥር ስር ይሁን። የማምለጫ መንገድዎ ዋናው የሚያነጣጥሩበት እይታዎ ይሁን። ከአደጋው እንዳመለጡ ተቃራኒውን የሀንድግሪፕ ይጫኑ። አቅጣጫዎን በፍጥነት ወደግራ መቀየር ቢፈልጉ የግራውን ሀንድግሪፕ ይጫኑትᎾ ወደነበሩበት ለመመለስ ሲፈልጉ ደግሞ ቀኙን ይጫኑ። ወደቀኝ መቀየር ቢፈልጉ የቀኙን ሀንድግሪፕ ይጫኑትᎾ ወደነበሩበት ለመመለስ ሲፈልጉ ደግሞ ግራውን ይጫኑ።

ፍሬን መጠቀም ቢያስፈልግ አቅጣጫን በፍጥነት ከመቀየር ይቆጠቡ። አቅጣጫን በፍጥነት በሚቀይሩበት ወቅት ሳይሆን፣ ከዚያ አስቀድመውና በኋላ ብሬክ ይጠቀሙᎾአቅጣጫን በፍጥነት በሚቀይሩበት ወቅት ግን ፈጽሞ አይሁን።

ኮርነሪንግ

በነጠላ አሽከርካሪዎች ላይ የሚደርሰው አደጋ ዋንኛው ምክኒያት የሞተር ሳይክሎች በሰፊ ከርቭ ማድረግ ወይም መዞርና ከተሽከርካሪዎች መንገድና ከቋሚ ነገሮች ጋር የሚደርግ ግጭት ናቸው።

እያንዳንዱ ከርቭ የተለያየ ነው። የሚያጋጥምዎትም ከርቭ ባለበት ሁኔታ የሚቀጥል(ኮንስታንት ከርቭስ) ከሆነ፣ ቀስ በቀስ የሚሰፋ ከሆነ፣ ጠበብ ብሎ የሚቀጥል ከሆነ፣ በርካታ ማዞሪያዎች(ማልቲፕል ከርቭስ) እንዳሉት በንቃት ይቆጣጠሩ።

በችሎታዎ ልክ አንዲሁም በተፈቀደው የፍጥነት ልክ ያሽከርክሩ።

የበለጠ ነው ብለው የመረጡት መንገድ ሁልጊዜ የመንዱን ከርቭ ላይኩል ይችላል።





የሌይን ለውጥ በትራፊክ ፍሰት፣ በመንገዱ ሁኔታና ከርብቸ ልይ የተመሰረተ ነው። የትራፊክ ፍሰት ከሌለ የእይታዎን መጠንና በአስተማማኝነት ለመዞር የሚስችልዎትን ራዲየስ ለመጨመር እንዲችሉ ከከርቡ ውጭ ይጀምሩ። በሚዞሩበት ወቅት ወደ ውስጠኛው ከርብቸ ይሂዱ፤ መሀሉንም እንዳለፉ ወደውጭ በመውጣት ወደ ኤግዚት ይውጡ።

ሌላው አማራጭ ወደ ከርብቸ ከመግባትዎ በፊት ወደ ሌይኑ መሀል ይግቡ፤ ኤግዚት እስከሚያደርጉ በዚያ ይቆዩ። ይህም የሚቀርብዎትን የትራፊክ ፍሰት በቶሎ አንዲያውቁ ያስችልዎታል። ባሉበት ሌን ላይ በመሀል መስመር ላይ ሊኖር የሚችለውን የትራፊክ መጨናንቁንም ወይም ሊያሰናክልዎት የሚችለውን የተጣለ ነገርም ከግምት አስገብተው ይለፉ።

8	*እራስዎን ይፈትኑ*

በፍጥነት ለማቆም የበለጠው መንገድ :

ሀ.የፊቱን ብሬክ ብቻ ይጠቀሙ።

ለ. የኋላውን ብሬክ

በመጀመሪያ ይጠቀሙ

ሐ. ስሮትሉን ወደታች ማድረግና የፊቱን ብሬክ መጠቀም።.

መ. ሁለቱንም ብሬክስ በአንድ ላይ ይጠቀሙ።.

መልስ - ገጽ 40

አደገኛ የመንገዶችን ላይ ማለፍ

አደጋ ላይ የመውደቅ ወይም ቦጭት ላይ የመሳተፍ እድልዎ ከፍ የሚለው በሚከተሉት ላይ ሲያሽከረክሩ ነው።

- **ምቹ ያልሆኑ መንገዶችና እንቅፋቶች**
- **በሚያንሸራትቱ መንገዶች ላይ**
- **የባቡር ሀዲዶች ላይ**
- **በረጅምና ጠባብ መተላለፊያ (ግሩቭስ) ወይም የመንገድ አጥር (ግሬቲንግስ)**

ምቹ ያልሆኑ መንገዶች ወይም እንቅፋቶች

ምቹ ያልሆኑን መንገዶች እንደባሞፕ፣ የተሰበረ ፔይቭመንት፣ ፓትሆልስ፣ ትናንሽ የህይዌይ ቆሻሻዎች ያጠኑ። እንቅፋቶችን ፍጥነትዎን በመቀነስ ወይም በዙሪያቸው በማለፍ አንቅፋቶችን ማስወገድ ይችላሉ። በተጋጠምዎት አንቅፋት ላይ የግድ መሄድ ካለብዎት በመጀመሪያ በዚያ መሄድ እንደሚችሉ ያረጋግጡ ።ብተቻልዎት መጠን በ90° ማእዘን ይጠጉት። የሚሄዱበትን መንገድ ለመቆጣጠር ይችሉ ዘንድ መሄድ ወደ ፈለጉበት ይመልከቱ። በእንቅፋቱ ላይ መሄድ ካለብዎት ማድረግ ያለብዎት ይህ ነው፤

- ከመንካትዎ በፊት በተቻልዎት መጠን ፍጥነትዎን ይቀንሱ
- ሞተር ሳይክልዎ ቀጥ ብሎ እንድሚሄድ ያረጋግጡ።

ቅፋቶች



- ክብደትዎን በእግር ማስቀመጫ ላይ እንደሚሆን አድርገው **በትንሹ ከተቀመጡበት ከፍ ይበሉ**። ይህም የግጭቱን ሀይል በአብራክዎና በክርንዎ ለማስቀረት ያስችልዎታል፤ ከሞተር ሳይክሉም ላይ እንዳይወድቁ ይረዳዎታል።

- **ከመንካትዎ በፊት** ስሮትሉን በትንሹ ያሽከርክሩት,ይህም በፊት ለፊት በኩል ባለው ጫፍ ቀለል ያለ ሁኔታ ለመፍጠር ይጠቅማል።

በመንገድ ላይ ባለ ነገር ላይ ከሄዱ ለሌላ ጉዞ ከመጀመርዎ በፊት መንገድ ዳር ይሂዱና የሞተርሳይክልዎን ጎማዎችና የጎማዎቹ ማሽከርከሪያዎች ጎዳት ደርሶባቸው እንደሆነ ይቆጣጠሩ ።

የሚያንሸራትት መሬት

ሞተርሳይክሎች ተሽከርካሪን በሚይዝ መሬት ላይ በጥሩ ሁኔታ ሊሽከረከሩ ይችላሉ። አነስ ያለ የመያዝ ሁኔታ ያላቸው መሬቶች የሚጠቃልሉት፡

- **እርጥብ ፔቭመንት**፡ በተለይ መዝነብ ከጀመረ በኋላ።እንዲሁም የመሬት ላይ ዘይት ታጥቦ ወደ መንገዱ ጥግ መሰብሰብ ሲጀምር።
- **የግራቨል መንገዶች** ወይም አፈርና ግራቨል ሲሰበሰቡ።
- **ጭቃ፣ውርጭ ወይም በረዶ**።
- **የሌይን ምልክቶች(የተቀቡ መሬቶች)** የመንገድ ላይ የብረት ንጣፎች(ስቲል ፕሌትስ)፣ ማስተላለፊያዎችን ለመቅበር ተቆፍሮ የተሸፈነ መሬት ፤በተለይ እርጥብ በሚሆንበት ጊዜ።

በሚያንሸራትት መንገድ ላይ ለማሽከርከር ፡

- **ፍጥነት መቀነስ** – የመንሸራትት እደልዎን ለመቀነስ ወደ አንሸራታቹ መሬት ከመድርስዎ በፊት ፍጥነትዎን ይቀንሱ። የሚጓዝ ሞተርሳይክልን ለማቆም ተጨማሪ የማቆሚያ ጉዞ አስፈላጊ ነው።በተለይ ወደ እርጥብ ከርቭ ከመግባትዎ ፍጥነትዎን መቀነስ አስፈላጊ ነው።
- **የድንገት እንቅስቃሴን ያስወግዱ**

በድንገት የሚደረግ የፍጥነት ወይም የአቅጣጫ ለውጥ መንሸራተት ሊያስከትል ይችላል።ፍጥነት በሚጨምሩበት ወቅት፣ ጊርስ በሚለውጡበት ወቅት፣ በሚዞሩበት ጊዜ ወይም ብሬክ ሲጠቀሙ በተቻልዎት መጠን በተረጋጋ ሁኔታ ያድርጉት ።

- **ሁለቱንም ብሬኮች ይጠቀሙ** – የፊቱ ብሬክ በአንሸራታች መሬት ላይም ቢሆን ውጤታማ ነው።

የብሬክ ሊቨርን ቀስ በቀስ ጭምቅ ያድርጉት። ይህም የሞተርዎን የፊት ተሽከርካሪ እንዳይቆለፍ ይረዳል። ያስታውሱ የኋላውን ብሬክ ግፊት ሲጠቀሙ ቀስ በቀስ ይሁን።

- **የሌይኑን የመሀል ቦታ** በሚረጥብበት ጊዜ አደገኛ ነው።መዝነብ በሚጀምርበት ጊዜ የመኪናዎች የጎማ ምልክት ባለበት መንገድ ላይ ያሽከርክሩ።አብዛኛውን ጊዜ የግራው የመኪናዎች የጎማ ምልክት ያለበት ስፍራ የበለጠው ቦታ ነው፤ በተጨማሪ የትራፊኩ ፍሰትና ሌሎች የመንገዱ ሁኔታም ይወስነዋል።
- **ዘይት የፈሰሱባቸውን ቦታዎች ይመልከቱ** ጉዞዎትን ለመግታት ወይም ለማቆም ሲፈልጉ እግርዎትን ያወርዳሉ።በዚህ ጊዜ ሊንሸራተቱ ወይም ሊወድቁ ይችላል።
- **በመንገድ ዳርና ዳር የተሰበሰበ ቆሻሻና ግራቨል** በተለይ ከሀይዌይና ወደ ሀይዌይ የሚሄዱ ከርቮችና ራምፖች ላይ አንዲሁም በመንገዱ ዳር ምን እንዳለ ይወቁ፤ በተለይ በጠባቡ ሲዞሩና በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ነጻ ሀይዌይ ሲወጡና ሲገቡ።
- አንዳንድ የመንገዱ ክፍሎች ከሌላው የመንገዶች ክፍል ይልቅ **ዝናብ በቶሎ ሲደርቅ ውርጭ በቶሎ ይቀልጣል**። የውርጭ ክምችት የሚበዛው በዝቅተኛ ወይም በተሸፈኑ ቦታዎች እንዲሁም በድልድዮች ላይና የላይ መተላለፊያዎች(በኦቨርፓሶች) ላይ ነው።
  እርጥብ መንገዶች ወይም እርጥብ ቅጠሎችም አንሸራታቾች ናቸው። ዝቅተኛ መንሸራተት ባለበት የሌይኑ ቦታ ላይ ያሽከርክሩ። ፍጥንትዎንም ይቀንሱ።

ጠንቃቃ አሽከርካሪዎች ከበረዶና ከውርጭ በነጻ መንገድ ያሽከረክርሉ። የግድ በአንሸራታች መሬት ላይ ማሽከርከር ካለብዎት ሞተርሳክልዎን ቀጥ አድርገው በመንዳት ይጓዙ አንዲሁም በተቻልዎ መጠን ፍጥነትዎን ይቀንሱ። ተልቅ ያለ አንሸራታች መንገድ ካጋጠምዎትና በቀስታ እንዲጓዙ ወይም በእግር እርምጃ ፍጥነት እንዲጓዝ ግድ ከሆነብዎት እግሮችዎን መሬት ላይ በማድረግ በቀላሉ ሊያልፉት ይችላሉ። ሞተር ሳይክሉም መውደቅ ከጀመረ ራስዎን በመያዝ ማጽንት ይችላሉ። ብሬክስ ግን አለመጠቀምዎን ያረጋግጡ። ከተቻልዎት ክላቹን ጨምቀው በመያዝ ቀስ ብለው ይሂዱ። ይህን አንቅስቃሴ በጣም ዝቅተኛ ከሆነው የፍጥነት ልክ ሌላ ከሞከሩ አደጋ እንዲሚመጣብዎት ይወቁ።





የባቡር ሀዲዶች፣የትሮሊ ሀዲድ ና የፔይቭመንት መከለያዎች(ሲምስ)

ትራኮችን ለማቋረጥ አብዛኛውን ጊዜ ባሉበት ሌይንብበቀጥታ ማሽከርከር አስተማማኝ ነው። ከፊትዎ ያለ ትራክን ለመዞር (በ 90° ማእዘን) ለማለፍ መሞከር አደገኛ ሊሆን ይችላል። መንገድዎ ወደሌላ የትራፊክ ሌይን ሊመራዎት ይችላል።

ባሉበት መንገድ ትይዩ ያሉትን ሀዲዶችና የመንገድ መከለያ (ሲምስ) ከሀዲዱ፣ ወደ ታች ከሰመጠ መንገድ፣ የፔቭመንት(መከለያ) ሲምስ ለማቋረጥ ቢፈልጉ ራቅ ይበሉና ቢያንስ ብ45° ማእዘን ያቋርጡት።





ከዚያም በፍጥነትና በጠባቡ ይዙሩ። በጠርዙ ላይ መሄድ ጎማዎትን ሊይዝብዎትና ከሞተርሳይክልዎ ላይ ሊጥልዎት ይችላል።

ግሩቭስ እና ግሬቲንግስ

በዝናብ ግሩቭስ ወይም በድልድይ ግሬቲንግስ ላይ ማሽከርከር ሞተርሳይክልን ሊያውዛውዝ ይችላል። ይህ ቀላል ያልሆነ የመንቀሳቀስ ስሜት በአጠቃላዩ አደገኛ አይደለም። ዘና ብለው በአንድ ወጥ ፍጥነት በመጓዝ በቀጥታ አልፈው ይሂዱ። ማእዘን ፈጥረው ለሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች በሌይኑ ላይ እንዲቆዩ ዚግዛግ(ወዲያና ወዲህ)እንዲሉ ያስገድዳቸዋል። የዚግዛግ(ወዲያና ወዲህ) የማለቱ ስሜት ከመወዝወዙ ጋር ሲወዳደር በጣም አደገኛ ነው።





9 እራሳዎን ይፈትኑ

መዘነብ ሲጀምር አብዛኛውን ጊዜ

ሀ.በሌይኑ መሀል ያሽከርክሩ።

ለ. ዝናቡ እስከሚቆም ወደ መንገዱ ዳር መኪናዎን ያስጠጉ።

ሐ. መኪናዎች በተሽከረከሩበት አሻራ ላይ ያሽከረከሩት።

መ.ፍጥነትዎን ይጨምሩ።

መልስ - ገጽ 40

ትይዩ ሀዲዶች-ስህተት/ሜካኒካዊ (የሞተሩ አሰራር) ችግሮች

ሞተርሳይክሎዎ በሚሸሽበት ወቅት በአስቸጋሪ ሁኔታ ወዛዋ ይወድቃሉ። ይህን ሜካኒካዊ ችግር ለመፍታት ሲሞክሩ ወቅት የሚያጋጥዎትን የመንገዱንና የትራፊክ ፍሰቱን ሁኔታዎች ከግምት ያስገቡት። ቀጥሎ የተጠቀሱት መምሪያዎች ሜካኒካዊ ችግሮችን በአስተማማኝ መልኩ ለመፍታት ያስችልዎታል።

የጎማ መበላሸት

አልፎ አልፎ ጎማ እንደሚተፋስ ይሆማል። ሞተርሳይክልን ሲያዝት ለይት ለይት ያለ ስሜት ከፊጠረብዎት የጎማ ችግር ሊሆን ይችላል። ይህም አደገኛ ሊሆን ይችላል።ሞተርሳይክሉ ከሚያሳየው ባህሪይ ተነስተው ችግሩን ማወቅ አለብዎት። ከጎማዎችዎ አንዱ አየሩ ቢተነፍስ፡ ሚዛንዎን ለመጠበቅ እርምጃ ይውሰዱ። ከመንገዱ ወደ ዳር አቁመው ጎማዎቹን ይቆጣጠሩ።

ከፊት ያለው ጎማ ከተነፈሰ ማሽከርከሩ "ከባድ" ይሆናል። የፊቱ ተሽከርካሪ ሲተነፍስ በተለይ አደገኛ ይሆናል። ምክኒያቱም የማሽከርከርዎን ሂደት ተጽእኖ ያደርግበታል። ሚዛንዎን ለመጠበቅ በጥሩ ሁኔታ ማሽከርከር ያስፈልግዎታል።

የኋለውጎማ ከዘፈፈሰ የሞተርሳይክሉ የኋለኛ ክፍል መንቀጥቀጥ ወይም ከሸንወደ ጎንለመዝወዝ ይችላል።

በሚያሽከረክሩበት ወቅት ሁለቱም ጎማዎች ከተነፈሱ:

- **ሀንድግሪፕስን አጥብቀው ይያዙ፣** ስሮትሉን ልቀቅ ያድርጉት እንዲሁም ቀጥ ያለ መንገድ ይጓዙ።
- **ብሬኪንግ(ማቆም) ካስፈለገ** ግን ያልተነፈሰውን ጎማ ብሬክ ይጠቀሙ፣የትኛው አንደተነፈሰ ግን እርግጠኛ ይሁኑ።
- **ሞተርሳይክልዎ ፍጥነቱን ሲቀንስ** ወደ መንገዱ ዳር ተጠግተው ክላችቹን ጭምቅ በማድረግ ያቁሙ።

ስታክ (የማይንቀሳቀስ) ስሮትል

የስርትሉ ኬብል ካልተንቀሳቀሰ። ስሮትሉን ወደ ኋላና ወደ ፊት ደጋግመው ያዙሩት። ይህም እንዲንቀሳቀስ ሊያስችለው ይችላል። ስሮትሉ ባይንቀሳቀስ በቶሎ የኤንጅን ካት አፍ ስዊችን ይጠቅሙ እንዲሁም ክላቹንም ይሳቡት። ይህንንም በአንድ ላይ ያደርጉት። ይህም ሀይሉን ከኋላ ጎማ ያስወግደዋል፤ የሞተሩ ድምጽ በቶሎ ባይጠፋም። ሞተርሳይክሉን "በቁጥጥር ስር" ካዋሉት ወደ መንገድ ዳር ሄደው ያቁሙ።

እንዳቆሙም የስሮትሉን ኬብል በጥንቃቄ በመቆጣጠር የችግሩን መነሻ ያግኙ። አንደገና ማሽከርከር ከመጀመርዎ በፊት ስሮትሉ እንደሚሰራ ያረጋግጡ።

መወዛወዝ

"መወዛወዝ" የሚያጋጥመው የፊት ተሽከርካሪውና ሀንድልባርስ በድንገት ከጎን ወደ ጎን በአንድ አይነት ፍጥነት መንቀጥቀጥ ሲጅምሩ ነው። አብዛኛዎች መውዛወዝ ከማይገባ ጭነት፣ ተስማሚ ካልሆኑ አክሰሰሪዎች ወይም ከተሳሳተ የጎማ ግፊት ይመጣል። ከባድ ጭነት ከተሸከሙ ያቅልሉት።ካልተቻለም ይቀይሩት። ክብደቱን ወደመሀል ዝቅ አድርገው ወደ ሞተርሳይክልዎ ወደፊት ያድርግጉት። የጎማው ግፊት መጠን፣ ስፕሪንግ ፕሪሎድ፣ የአየር ሾክ እንዲሁም ዳምፐርስ ለክብደቱ ተስማሚው ልክ ስለ መሆናቸው ያረጋግጡ። የንፋስ መከላከያዎቹና ፌይሪንግስ በትክክል መቀመጣቸውን ያረጋግጡ።

ባልተስተካከለ መልኩ የተገጠሙ የተሽከርካሪውን ክፍል እንዳለ ያረጋግጡ፤ የተዳከመ የተሽከርካሪ ክፍሎችን፣ የተጣመመ የፊት ተሽከርካሪ፣ መሆን ካለበት ቦታ የተዛነፈ ወይም ከሚገባው ቦታ ውጭ ያለን፣ የላላ የ ዊል ቢሪንግስ ወይም ስፖክስ፣ እንዲሁም የተዳከመ ስዊንግአርም ቢሪንግስ እንዳለ ያረጋግጡ። የችግሩ መንስኤ ከእነዚህ አንዱ ካልሆነ ሞተርሳይክልዎን በአጠቃላይ በባለሞያ ያስመርምሩ።

"ከመውዛውዝ ወደ ፍጥነት መጨመር" ለመሸጋገር ቢሞክሩ የሞተርሳይክልዎ አለመረጋጋት ነው የሚከተለው። ይልቁንም

- **ሀንድልባሩን በጽኑ ይያዙት።** ነገርግን መውዛወዙን አይታገሉት።
- **ፍጥነትዎን ለመቀነስ ስሮትሉን ቀስ በቀስ ይዝጉት።** ብሬክስ አይጠቀሙ።ብሬክስ መወዛውዙን የባሰ ሊያደርገው ይችላል።
- **ክብደትዎን** ወደ ፊትና ወደታች በተቻለ መጠን **ያንቀሳቅሱት ።**
- **ከመንገዱ ዳር መኪናዎን ያስጠጉና** በቶሎ ችግሩን ያስተካክሉ።

10	እራስዎን ይፈትኑ
ሞተርሳይክል መወዛወዝ ከጀመረ፥	
ሀ.ፍጥትነትዎን በመጨመር ከመወዛወዙ ይውጡ።	
ለ.ብሬክስን ቀስ በቀስ ይጠቀሙ	
ሐ.ሀንድልባርስን በጽኑ ይዘው ስሮትሉን ቀስ በቀስ ይዝጉት።	
መ. ፍጥንትዎን ይቀንሱ	
	መልስ -ገጽ 40

የሰንሰለት ችግሮች

በሚያሽከረክሩበት ወቅት የሚንሸራተት ወይም የሚሰበር ሰንሰለት የኋላ ተሽከርካሪውን ሊቆልፈው ወይም ሳይክልዎን ሊያንሸራትት ይችላል። የሰንሰለት መንሸራተት ወይም መሰበር በተገቢ ጥገና ሊስተካከልና ሊወገድ ይቻላል።

- **መንሸራተት፥** ሰንሰለቱ የሚንሸራተተው ፍጥነት በቶሎ ለመጨመር በሚሞክሩበት ወቅት ወይም ከፍታን ለመውጣት ወይም ወደ መንገድ ዳር ሲጠጉ ነው።ሰንሰለቱንና ሰንሰለቱ የሚዞርበትን መዞሪያዎች ይቆጣጠሩ። ሰንሰለቱን ማጥበቅ ለችግሩ መፍትሄ ሊሆን ይችላል።ችግሩ ከተበላሸ ወይም ከተወጠረ ሰንሰለት ከሆነ ወይም የተጣመሙ የሰንሰለቱ መዞሪያዎች ከሆነ ሰንሰለቱን ወይም ሰንሰለቱ የሚዞርበትን መዞሪያዎች ወይም ሁለቱንም እንደገና መቀየር ያስፈልጋል።
- **መሰበር፥** በሞተሩ የኋላ ተሽከርካሪ ላይ ወዲያውኑ የሀይል ማጣት እንዳለ ያውቃሉ። ስሮትሉን በመዝጋት ለማቆም ብሬኩን ይጠቀሙ።

የኤንጅን መቆም

ኤንጅኑ "በሚቆለፍበት" ወይም በሚዘጋበት" ጊዜ በአብዛኛው ጊዜ ምክኒያቱ የአይል ማነስ ነው። የሚንቀሳቀሱት የኢንጅኑ ክፍሎች እርስበራሳቸው እየተጋገዙ በሰከነ ሁኔታ አይንቀሳቀሱም፤ ኤንጅኑም ከመጠን በላይ ይግላል። የመጀመሪያው ምልክት የኤንጅኑ ሀይል መጥፋት ወይም የኤንጅኑ ድምጽ መለወጥ ሊሆን ይችላል።የክላቹን ሊቨር በመጭመቅ ኤንጅኑን ከኋልኛው ተሽከርካሪ ጋር ያለውን ግንኙነት ያቋርጡት።ወደ መንገዱ ዳር ይጠጉና ያቁሙ። አይሉን ይቆጣጠሩ። አስፈላጊ ከሆነም አይል በተቻለ ፍጥነት መጨመር ።ይህ ካልሆነ ኤንጅኑ ይቆማል።ይህ ሲሆን የሚከተለው ነገር ልክ የኋላው ተሽከርካሪ እንድተቆለፈ ይሆናል። እንደገና ከመንቀሳቀስዎ በፊት ኤንጅኑ መቀዝቀዝ ያስፈልገዋል።

እንሰሶች

እንደሚታወቀው እንሰሶችን እንዳይገጩ ድህንነት በሚጠብቅ ሁኔታ የተቻልዎት ማድረግ ያስፈልጋል። በትራፊክ ፍሰት ውስጥ ካሉ ግን ባሉበት ሌይን ላይ ይቆዩ። አነስ ያለ ነገር መግጨት ከትልቅ ነገር (አንደመኪና የመሳሰሉትን) መግጨት አነስ ያለ አደጋ አለው።

ሞተርሳይክሎች ውሾችን የሚማርኩ ይመስላል።በውሻ ቢባረሩ ፍጥነትን አቀዝቅዘው ወደ እንሰሳው በቀስታ ይጠጉ።አንደተጠጉም ፍጥነትዎን ጨምረው እንሰሳውን ከኋላ ትተውት ይሂዱ።እንሰሳውን ለመራገጥ አይሞክሩ። ሞተርሳይክሉን ይቆጣጠሩና መሄድ ወደ ሚፈልጉበት ይመልከቱ።

ለትላልቅ እንሰሶች ማለትም እንደ ዲር፣ ኢልክ፣ ከብት ላሉት ብሬክ በመጠቀም ለመቆም ይዘጋጁ፤ እንሰሶቹ ምን እንደሚያደርጉ አይታወቅምና።

11	እራስዎን ይፈትኑ
በውሻ ቢባረሩ:	
ሀ. በእርግጫ ይምቱት።	
ለ. ውሻው ፍላትቱ አስኪቀንስ ድረስ ያቁሙ።	
ሐ. በእንሰሳው ዙሪያ ባልተረጋጋ አካሄድ ይጓዙ	
መ. እንሰሳውን በቀስታ ይጠጉት፤ ከዚያም ፍጥነት ይጨምሩ።	
	መልስ -ገጽ 40

የሚበሩ ነገሮች

ከጊዜ ወደጊዜ አሽከርካሪዎች በነፍሳት፣ ከመኪናዎች በሚወረውሩ ሲጋራዎች፣ ወይም ከፊት ካለ አሽከርከሪ በጎማዎች ከሚስፈነጠሩ ጠጠሮች ይመታሉ። የፊት መከላከያ ከለበሱ መከላከያው ሊበላሽ ወይም ሊሰነጣጣቅ ይችላል፤ ወይም ለማየት ሊከብድ ይችላል። ያለፊት መከላከያ ካሽከረከሩ የሚመጣው ነገር ዓይንን ፊትን ወይም አፍን ሊመታ ይችላል። ማንኛውም ነገር ቢሆን ዓይኖችዎን ከመንገድ እጆችዎንም ከሀንድልባስ አይለዩ። ሰላማዊ ሲሆንም ወደመንገዱ ዳር ሆነው የተበላሸብዎትን ነገር ያስተካክሉ።

ከመንገድ መውጣት

ከመንገድ ወጥተው ሞተርሳይክልዎን መቆጣጠር ቢፈልጉ(ወይም ለአጭር ቆይታ ማረፍ ቢፈልጉ) ማረጋገጥ ያለብዎት ነገር ቢኖር:

- **የመንገዱን ዳር ይቆጣጠሩ፣** የመንገዱ ዳር በላዩ ላይ ሆነው ለማሽከርከር አቅም እንዳለው ያረጋግጡ፤ ለስላሳ እንደሆነ፣ ወይም ሳር፣ ወይም ለስላሳ አፈር እንደሆነ ወይም ምን እንደሆነ ካላወቁ በነገሩ ላይ ከማሽከርከርዎ አስቀድመው ፍጥነትዎን ይቀንሱ።
- **ምልክት**– ካሉበት በኋላ ያሉት አሽከርካሪዎች ፍጥንነት ይቀንሳሉ ብለው ላይጠብቁ ይችላሉ ግልጽ ምልክት በመስጠት እንደሚያቀዝቅዙና አቅጣጫ አንደሚቀይሩ ያሳውቁ። ከመንቀሳቀስዎ አስቀድሞ መስተዋትዎን ይቆጣጠሩ እንዲሁም በራስዎ ይመልከቱ።

  ከመንገድ መውጣት – የሚችሉትን ያህል ከመንገድ ይውጡ። በመንገድ ዳር ያለን ሞተርሳይክል ለመለየት በጣም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ወዳሉበት ሌላ ሰው ተሽከርካሪውን እንዲያስጠጋ አያስፈልግዎትም።
- **በጥንቃቄ ያቁሙ** – ለስላሳ ወይም ያጋደለ የመንገድ ዳርቸዎች በዳር ወይም በመሀል ላይ የሚደረግን መቆም አስቸጋሪ ሊያደርጉት ይችላሉ።

ተሳፋሪዎችንና ጭነት መሸከም

ልምድ ያላቸው አሽከርከሪዎች ብቻ ተሳፋሪዎችን ወይም ትልቅ ጭነቶች መሸከም ይኖርባቸዋል። ተጨማሪው ክብደት የሞተርሳይክሉን አያያዝ፣ ሚዛን፣ የፍጥነት መጨመርንና መቀዝቀዝን ሊለውጠው ይችላል።ተሳፋሪ ከማሳፈርዎ በፊት ወይም ከባድ ጭነት ከመጫንዎ በፊት ከትራፊክ ፍሰት ውጭ ሆነው ይለማመዱ።

እቃዎች

ተሳፋሪዎችን በደህንነት ለመሸከም:

- ሞተርሳይክልዎን ተሳፋሪ ለመጫን እንደሚያስችል እቃዎችን **ያሰናዱና ያመቻቹ።**
- መንገድ ከመጀመርዎ በፊት **ተሳፋሪውን መመሪያ ይስጡት።**
- የማሽከርከር ቴክኒክዎን ተጨማሪ ክብደት ለማሽከርከር እንዲያስችል **አድርገው ያስተካክሉ።**

መሟላት ያለባቸው እቃዎች:

- **ተስማሚ መቀመጫ፣** ሁለታችውንም ለመያዝ በሚበቃ ልክና በማያጨናንቅ መልኩ መተለቅ አለበት። መቀመጥ ከሚገባዎት ወደፊት መጠጋት አያስፈልግም።
- ለተሳፋሪዎች የሚሆን **የእግር ማስቀመጫዎች፣** ጽኑ የእግር ማስቀመጫዎች ተሳፋሪው **እንዳይወድቅና እንዳይጎትትዎት** ይረዳል።
- **የመከላከያ እቃዎች** ፡ ለአሽከርካሪዎች የተጠቆመው ዓይነት የመከላከያ አልባሳት ተሳፋሪዎችም እንዲለብሱ ያስፈልጋል።

የሞተርሳክሉን ተጨማሪ ክብደት የመሸከም አቅም እንዲኖረው አድርገው ያስተካክሉት። ተሳፋሪ የሚጭኑ ከሆነ ለጎማዎቹም ተጨማሪ የግፊት ፓውንዶች መጨመር ያስፈልግዎት ይሆናል። (ለተሟላ አሰራር የንብረት ባለቤቱን መመሪያ ይመልከቱ።)ተሳፋሪው ከርስዎ ጋር በመቀመጫ ላይ በሚሆንበት ወቅት መስትዋቱንና የፊት መብራቱን ከሞተርሳይክሉ የማእዘን ለውጥ ጋር እንደሚመች አድርገው ያስተካክሉ።

ተሳፋሪዎችን መመሪያ መስጠት

ተሳፋሪዎም የሞተርሳይክል አሽከርካሪ ቢሆንም መጓዝ ከመጀመርዎ በፊት የተሟላ መመሪያ መስጠት ያስፈልጋል። ለአሽከርካሪዎ መንገር የሚያስፈልግዎት ነገሮች፡

- ኤንጅን ከተነሳ በኋላ ብቻ ሞተርሳይክልዎ ላይ **መውጣት ይገባል።**
- ሳያጨናንቅዎት በተቻለ መጠን **ወደፊት አንዲቀመጥ።**
- **ወገብዎን** በጥብቅ ይያዝ፣ዳሌ፣ ቀበቶ፣ ወይም የሳይክሉን ተሳፋሪ ሀንድሆልድን **በጥብቅ መያዝ ።**
- **ሁለቱንም እግሮችዎን እግር** ማስቀመጫው ላይ ማኖር ያስፈልጋል፤ በሚቆምበትም ጊዜም ቢሆን።
- **እግሮችን** ከጭስ ማውጫ(ዎች) ላይ፣ ከሰንሰለት ወይም ከሚንቀሳቀሱ **ነገሮች ማራቅ።**
- **በሚያጋድሉበት ወቅት ከርስዎ ጋር ከኋላዎ ማጋደል ያስፈልጋል።**
- **የማያስፈልግ ንግግር ወይም እንቅስቃሴማስወገድ።** *በተጨማሪ ለተሳፋሪው በሚከተሉት ሁኔታዎች የያዘውን(ችውን) እንዲያጠብቅ (እንድታጠብቅ) መናገር:*
- የመንገድ ላይ ችግሮች **በሚጠጉበት** ወቅት።
- ከማቆሚያ ቦታ **በሚነሱበት ወቅት።**
- ድንገተኛ አንቅስቃሴ በሚያደርጉበት ወቅት **ማስጠንቀቅ ።**

ከተሳፋሪዎች ጋር አብሮ ማሽከርከር

ሞተርሳይክልዎ የሚጓዝ ተሳፋሪ ከተሸከመ ቀዝቀዝ ያለ ትግባሬ ይኖረዋል። ተሳፋሪዎ ክብደት ካለው ረዘም ያለ የፍጥነት መቀነሻና የፍጥነት መጨመሪያ ጊዜ ይወስዳል፤ በተለይ ለቀላል ሞተርሳይክሎች።

12	እራስዎን ይፈትኑ

ተሳፋሪዎች ማድረግ ያለባቸው:

ሀ.ሲያጋድሉ ማጋደል ያስፈልጋል።

ለ. የሞተርሳይክሉን መቀምጫ መያዝ።

ሐ.በተቻልዎትመጠን ወደ ኋላ ይቀመጡ።

መ. ፊጽሞ እንዳይይዝዎት።

መልስ -ገጽ 40

- በከርቦች፣ ኮርነሮች፣ ወይም ባምፖች፡ ላይ ሲሆን **በትንሹ ፍጥነትዎን ይቀንሱ።**
- ወደ ማቆምያ ሲጠጉ **አስቀድመው ፍጥነት ማቀዝቅዝ ይጀምሩ።**
- ወደ ፊትዎና ወደ ጎንዎ **አደጋን ለመከላከል የሚያስችል ተለቅ ያለ ክፍተት ይፍጠሩ።**
- መንገድ ለመሻገር፣ ወደ ትራፊክ ፍሰት ለመቀላቀል ወይም ለመግባት **ተለቅ ያለ ክፍተቶች ይጠብቁ።**

ተሳፋሪውን ወደመንገድ ዳር ሲጠጉ፣ በፍጥነት ሲያቆሙ፣ በጠባቡ ሲያዙሩ፣ በሀምፕ ላይ ሲሽከረክሩ ስላለው ልዩ ሁኔታ ያሳውቁ። ራስዎን በትንሹ በማዞር ያሰቡትን ይግለጹ። ነገር ግን ዓይኖች በፊትዎ ባለው በመንገድ ላይ ይሁኑ።

ሽክም መሸከም

አብዛኞቹ ሞተርሳይክሎች ብዙ ጭነት እንደማይሸከሙ ሆነው ነው የተሰሩት።በተገቢ ሁኔታ ከተቀመጠና ከተገጠመ ግን ትንንሽ ጭነቶች በደህንነት ለመሸከም ይቻላል።

- **ጭነቱ አነስተኛ ይሁን።** ሽክሞችን በማይንቀሳቀስ በአስተማማኝ ሁኔታ በሳድልባግስ ውስጥ ያስቀምጧቸው።በሲሲባር ወይም በመቀመጫው ጀርባ መደገፊያ ላይ ሽክም መጫን የሞተርሳይክሉን የሴንተር ኦፍ ግራቪቲን ከመጨመሩ በላይ ሚዛኑን ያዛባል።

- **የጭነቱን ክብደቱን ወደፊት ማድረግ፡** የጭነቱን ክብደት በየኋላኛው አክሰል ላይ ወይም ከፊት ለፊት ያድርጉት። ታንክባግስ ጭነቱን ወደፊት እንዲሆን ያደርጋሉ። ነገርግን ጠንካራና ሹል ነገሮች ሲጭኑ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።ታንክባር ሀንድልባርን ወይም መቆጣጠሪያዎችን በቀላሉ ለማግኘት እንደማያስቸግር ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ከኋልኛ አክሰል በስተኋላ ጭነት መጫን የሞተርሳይክሉን የመዞርና የብሬክን ሁኔታ ላይ ተጽእኖ አለው። መውዛወዝ ሊያስከትል ይችላል።
- **ሽክሙን በተመጣጣኝ ሁኔታ አስተካክሎ ማስቀመጥ** – ሳድልባግስን አንድ ዓይነት በሆነ ክብደት መጫን ያስፈልጋል። ሚዛኑን ያልጠበቀ ጭነት ሞተርሳይክሉን ወደ አንድ ጎን አንዲዘነብል ያደርጋል።

- **ጭነቱን አስተማማኝ ማድረግ፡** ጭነቱን በኢላስቲክ ኮርዶች(ቡንጂ ኮርድስ ወይም ኔትስ) አጥብቆ ማሰር። ለአንድ ጎን ከአንድ በላይ የአታችመንት ነጥብ ባሉት የኢላስቲክ ኮርዶች መጠቀም ይበልጥ አስተማማኝ ያደርገዋል። የጠበቀ ጭነት በተሽከርካሪው ወይም በሰንሰለት ሊያዝና ሊቆለፍ እንዲሁም ሊንሸራተት አይችልም። ገመድ ከተዘረጋ ቋጠሮው ሊፈታና ጭነቱ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወድቅ ይችላል።

- **ጭነትን መቆጣጣር፡** ጭነቱ እንዳላላ ወይም እንዳልተንቀሳቀሰ ለማረጋገጥ አለፍ አለፍ ብለው ያቁሙና ይቆጣጠሩ።

በቡድን ማሽከርከር

ከሌሎች ጋር በቡድን ሲያሽከረክሩ ደህንነትዎን በሚያካልብትና በሌሎች የትራፊክ ፍሰት ውስጥ በመግባት ሳያስተካክሉ ያሽከርክሩ

ቡድኑን አሳንሶ መጓዝ

አነስተኛ ቁጥር ያለው ቡድን በዚያው አካባቢ ለሚንቀሳቀሱ የመኪና አሽከርካሪዎች ቀላል ያለና ለደህንነት የሚስማማ ነው። አነስተኛ ቁጥር ያለው ቡድን በትራፊክ ፍሰት ወይም በቀይ መብራት አይቋረጥም። አሽከርካሪዎች ለመድረስ ሁልጊዜ አይቻኮሉም።ቡድንዎ ከአራት ወይም ከአምስት በላይ ከሆነ ወደ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ትንንሽ ቁጥሮች ይከፋፍሉዋቸው።

ከቡድኑ ጋር በአንድነት መቆየት

- **ጀማሪዎችን ከፊት ያድርጓቸው ፡** ልምድየሌላቸውን አሽከርካሪዎች ከመሪው በኋላ ያድርጉ ስለዚህም ነው ልምድ ያላቸው አሽከርካሪዎች ከኋላ ሆነው ማየት ይችላሉ።
- **ከኋላ ያሉትን ይከታተሉ።** ከቡድኑ በስተመጨረሻ ያለው የፍጥነቱን አካሄድ ይወስኑ። መስተዋትዎን ተጠቅመው ከኋላዎ ያለውን ሰው ይከታተሉ **አንድ አሽከርካሪ** ወደኋላ ቢቀር እንያዳንዱ የቡድኑ አባል ፍጥነት በመቀነስ ወደኋላ የቀረውን አባል መጠበቅ አለበት።

- ***ያቅዱ፡*** መሪው ወደፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ለውጦች በማየትና “ቃሉ ተመልሶ ይመጣል እንደሚባለው አባባል” አስቀድሞ ምልክት በማሳየት ሁሉም የቡድኑ አባል ለውጡን እንዲያከናውን ያስችላል።

- **መንገድዎን ይወቁ፡** እያንዳንዱ አባል የሚሄድበትን መንገድ ማወቅ አለበት። ከዚያም አንዱ በነጠል ሌሎቹ እንዳይጠፉ ወይም በተሳሳተ ማዞር እንዳይዙሩ ፍጥነት መጨመር የለባቸውም። በረጅም ጉዞዎች ላይ ተደጋጋሚ ማቆምን ያቅዱ።

ርቀትዎን መጠበቅ

ተቀራርበው በደረጃ ይሂዱ። ነገር ግን በዚያው ጊዜ በአስተማማኝ የመጠባበቂያ ርቀት ላይ በመሆን እያንዳንዱ በቡድኑ ውስጥ ያለ አሽከርካሪ በጊዜና በቦታ አደጋዎችን ለመከላከል ያስችላል ።የተቀራረበ ቡድን በሀይዌይ ላይ አነስተኛ ቦታ ሲይዝ፣ ለማየትም ቀላል ሲሆን እንዲሁም የመነጣጠሉ ሁኔታም **አነስተኛ ነው። ነገርግን በተገቢው መንገድ** መሆን አለበት።

በጥንድ አይጓዙ፡ ከሌላ አሽከርካሪ ጎን አያሽከርክሩ። ከመኪና ወይም በመንገድ ካለ ነገር ማምለጥ ካለብዎት ቦታ አይኖርዎትም። ለማውራት ሁለታቸሁም ማቆም ይኖርባችዋል።

ስታገርድ ፎርሜሽኑ፡ ይህ የበለጠው በደረጃ ለመቀራረብና በቂ ርቀት ለመጠበቅ ያስችላል።



መሪው በሌይኑ በግራ በኩል ሲያሽከረክር ሁለተኛው አሽከርካሪ ከኋላ ሆኖ በሌይኑ በቀኝ በኩል ሆኖ ይከተላል።

ሶስተኛው አሽከርካሪም በግራ በኩል በመሆን ከመጀመሪያው አሽከርካሪ ጋር በሁለት ደቂቃ ልዩነት ይከተላል። አራተኛው አሽከርካሪም በሁለት ደቂቃ ልዩነት ሁለተኛውን አሽከርካሪ ይከተላል። ይህ አሰራር ቡድኑን እንዲቀራረብ ከመርዳቱ በላይ እያንዳንዱ አሽከርካሪ ከሌላው ከፊት ለፊት ካለው፣ ከኋላው፣ እንዲሁም ከጎኖች ካሉት አሽከርካሪዎች ጋር አስተማማኝ ርቀት እንዲኖረው ያስችላል።

- **ቅርጽ ሰርቶ ማለፍ** ፡በስታገርድ ፎርሜሽን የሚጓዙ አሽከርካሪዎች አንድ በአንድ ማለፍ ያስፈልጋቸዋል።
- **አስቀድሞ የመጀመሪያ መሪው ካለበት** በመውጣት ምቹ ሁኔታ በመጠበቅ ያልፋል። አልፎም እንደሄደ ወደነበረበት ግራው ከተመለሰ በኋላ በሚያልፍበት ወቅት በነበረበት ፍጥነት በማለፍ ለሚቀጥለው አሽከርካሪ ክፍት ቦታ ይስጠው።
- **የመጀመሪያው አሽከርካሪ በደህንነት እንዳለፈ** ሁለተኛው አሽከርካሪ ወደ ግራ በኩል ይለፍና ለማለፍ ምቹ ሁኔታ ይጠባበቅ ካለፈም በኋላ ወደ ቀኝ በኩል ተመልሶ ለሚቀጥለው አሽከርካሪ ክፍት ቦታ ይስጠው። አንዳንድ ሰዎች እንደሚጠቁሙት የፊት መሪው አሽከርካሪውን እንዳለፈ ወደ ቀኙ መሆን አለበት ይላሉ። ይህ ጥሩ ሀሳብ አይደለም። ምክኒያቱም ሁለተኛው አሽከርካሪ ከፊት ለፊት ካለው አሽከርካሪ ጋር ትልቅ አደጋ የማስወገጃ የመጠበቂያ ርቀት ከመፈጠሩ በፊት እንዲያልፍና እንዲያቋርጠው ያበርታታል። አሽከርካሪው ከማለፍ በፊት በነበረው ቦታ ላይ እንዲመለስ ቀላሉና አስተማማኙ መንገድ በቂ ቦታ እስከሚገኝ ድረስ መጠበቅ ነው።

ሲንግል-ፋይል ፎርሜሽን – በከርብ ላይ በሚያሽከረክሩበት ወቅት ፣ በማዞሪያ ላይ፣ ሀይዌይ ሲገቡና ሲወጡ በሲንግል ፋይል ፎርሜሽን መንቀሳቀሱ ይመረጣል።

13	እርስዎን ይሞክሩ

ልምድ የሌላቸው አሽከርካሪዎች በቡድን ሲያሽከረክሩ መያዝ ያለባቸው ቦታ:

ሀ. ከመሪው በኋላ

ለ. ከቡድኑ ፊት ለፊት

ሐ. ከቡድኑ በስተመጨረሻ

መ. ከመሪው ጎን

መልስ -ገጽ 40

***በቡድን ማለፍ** (ደረጃ 1)*



***በቡድን ማለፍ** (ደረጃ 2)*



ለማሽከርከር የሚመች የተስተካከለ ቅርጽ

ሞተርሳይክል ማሽከርከር ትኩረት የሚሻና የተወሳሰበ ስራ ነው። በማሽከርከር ችሎታው የተካኑ አሽከርካሪዎች ለአካባቢያቸውና ለማሽከርከሩ ስራ ትኩረት በመስጠት ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን በማወቅ፣ ጥሩ ውሳኔ በመወሰን፣ በቶሎና በብቃት በመተግበር ያሽከረክራሉ። ለሚለዋወጠው የመንገድና የትራፊክ ሁኔታ የርስዎ ድርጊትና አካሄድና ባልዎት ብቃትና ንቃት ይወሰናል። **አልኮሆልና ሌሎች እጾች ከሌሎቹ ይልቅ በትክክል** የማሰብና በደህንነት የማሽከርከር ችሎታዎን ይጎዳሉ። በትንሹ አንድ ብርጭቆ አልኮሆላዊ መጠጥ መጠጣት በድርጊትዎ ላይ ጉልህ አስተዋጾ አለው። አልኮሆላዊ መጠጥ ከጠጡ በኋላ ወይም እጽ ከወሰዱ በኋላ የሚኖሩትን አደጋዎች እንመልከት። እራስዎንና ተከታዮችዎን ከአደጋ ለመከላከል ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግዎትም ተጠንቷል።

ይህ እውቀት ለምን አስፈለገ?

ለሞተርሳይክል ግጭት ዋናው መንስኤ አልኮሆል ነው፤ በተለይም ገዳይ ለሆኑ ግጭቶች። ጥናቶች እንደሚያመልክቱት በሞተርሳይክል አደጋ ከሞቱት አሽከርካሪዎች ውስጥ ከ40%-45% የሚሆኑት የሞቱት በአልኮሆላዊ መጠጥ ምክኒያት ነው።ከነዚህ አሽከርካሪዎች አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት በደማቸው ወስጥ የሚገኘው የአልኮሆል መጠን ከህጋዊው መጠን በላይ **ነበር። የቀሩት ግን ትንሽ አልኮሆላዊ መጠጥ** ብቻ ነው የወሰዱት። ይህ ግን የመንዳት ብቃታቸውን ለመጉዳት በቂ ነበር። ባለፉት ጊዜያት የተወሰዱትን የእጽ መጠንን ለመለየት አስቸጋሪ ነበር ወይም ለትራፊክ ሪኮርድ የሚሆን ከመጠጥ ጋር በተያያዘ ከሚመጡ የህግ ጥሰቶች ለመለየት አስቸጋሪ ነበር። በአልኮሆል ወይም በእጽ "ተጽእኖ" ማሽከርከር ለእያንዳንዱ አሽከርካሪ አካላዊና ህጋዊ አደጋዎች አሉት።

አልኮሆላዊ መጠጥ መጠጣትና እጽ መጠቀም በመኪና አሽከርካሪዎች ላይ ትልቅ ችግር እንደሚኖረው በሞተርሳይክል አሽከርካሪዎች ላይም ትልቅ ችግር አለው። ነገር ግን በሞተርሳይክል አሽከርካሪዎች ላይ የመሞት ወይም ከባድ አደጋ የመድረሱ እድል ይበዛል ። የነገሮች ጉዳት ባለበት አደጋ ላይ የአደጋዎቹ 90% የሚደርሰው በሞተርሳይክል አሽከርካሪዎች ላይ ሲሆን 33% የሚሆነው አደጋ የሚደርሰው በመኪና አሽከርካሪዎች ላይ ነው። በአመታዊ ሲታይ 2,100 የሞተርሳይክል አሽከርካሪዎች ለሞት ሲዳረጉ ወደ 50,000 የሚሆኑት በዚሁ አደጋ ለከባድ ጉዳት ይዳረጋሉ። ይህን ስታትስቲክስ መናቅ በጣም አስቸጋሪ ነው።

ስለ አልኮሆላዊ መጠጥ መጠጣትና ሌሎች እጽ በመጠቀም የሚመጡትን ችግሮችን በተመለከተ እውቀት በማዳበር የማሽከርከርና የሳብስታንስ አቢይዝን **ቀላቅሎ መመልከት እንደማያስፈልግ ያስተውላሉ። አዎንታዊ** እርምጃ በመውሰድ እራስዎን ይጠብቁ ሌሎችም በአደጋ እራሳቸውን እንዳይጎዱ ይከላከሉ።

አልኮሆልና ሌሎች እጾች በሞተርሳይክል መንዳት ላይ ያለው ተጽእኖ

ማንም ሰው በአልኮሆልና በእጾች የሚመጣውን ችግር የመቋቋም አቅም የለውም። ጓደኛዎ አልኮሆላዊ መጠጥ እንዲሚቋቋም ወይም እጾች በመጠቀም የበለጠ መስራት እንደሚችል በጉራ ሊያወራ ይችል ይሆናል። ነገርግን አልኮሆልና እጾች በግልጽ የማሰብና የአካላዊ ስራዎችን በብቃት የማከናወን አቅምን ይቀንሳል። በማሽከርከሩ ተግባር ላይ የመወሰንና ውሳኔዎች የመተግበሩ ሂደት ከወዲሁ ህጋዊ ገደቡን ሳያልፉ ይስተጓጎላሉ።

አብዛኛዎቹ ኦቪር ዘ ካውንተር፣ ፕሪስክሪፕሽንና ህገወጥ እጾች በማሽከርከር ወቅት ሊደርስ የሚችለውን አደጋ እንዲጨምር ያደርጋሉ። እነዚህ እጾች በሞተር ሳይክል አደጋዎች ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ችግር ምን ያህል እንደሆነ በትክክል ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ነገርግን ሞተርሳይክል በማሽከርከሩ ሂደት ላይ የተለያዩ እጾች የሚያመጡት ችግሮች ማወቅ እንችላለን። የአልኮሆልና የሌሎች እጾች በጥምር የሚያስከትሉት ችግር በተናጠል ከሚመጣው ችግር ይልቅ በጣም አደገኛ ነው።

አልኮሆል በሰውነት ውስጥ

አልኮሆል በደም ዝውውር ውስጥ በቶሎ ይገባል። እንደሌሎቹ ምግቦችና መጠጦች መፈጨት አይሻም። **ከተወሰደ ከደቂቃዎች በኋላ ወደ አእምሮ ይደርስና ተጠቃሚ ላይ ተጽእኖ ያደርጋሉ።**

አልኮሆሉ የሚያስከትለው ዋና ተጽእኖ የሰውነትን ክንዋኔ(የአእምሮና የአካል)ማንተትና መጉዳት ነው። ማንኛቸውም የሚያከናውኑዋቸው ነግሮችን አልኮሆል ከወሰዱ በኋላ ባነሰ ብቃት ነው የሚከናውኗቸው።

በደም ውስጥ የሚገኘው የአልኮሆል መጠን

በደም ወስጥ የሚገኘው የአልኮሆል መጠን ወይም BAC ማለት በሰውነታችን ውስጥ ባለው ደም ውስጥ የሚገኘው የአልኮሆል መጠን ነው። በአጠቃላይ አልኮሆል ከሰውነታችን ውስጥ የሚወገደው ከሞላ ጎደል አንድ ብርጭቆ መጠጥ በአንድ ሰዓት ውስጥ ከተጠጣ ነው። ነገር ግን ሌሎች የተለያዩ ነገሮች ሰውነት ውስጥ የሚቀረውን የአልኮሆል መጠን ይወስኑታል። በደም ውስጥ የሚገኘው አልኮሆል ሲጨምር ነግሮችን ለማከናወን አለመቻሉም ይጨምራል።

በደም ወስጥ የሚገኘውን የአልኮሆል መጠን የሚወስኑ ሶስቱ ዋና ነገሮች:

- የወሰዱት **የአልኮሆል መጠን**
- **በምን ያህል ፍጥነት** እንደሚጠጡ
- **የሰውነትዎ** ክብደት

ሌሎች ነገሮችም አልኮሆል በሰውነት አሰራር ላይ ባለው ተጽእኖ ላይ የሚውስኑት ድርሻ አላቸው። ጾታ፣ አካላዊ ሁኔታና የምግብ አወሳሰድ በደም ወስጥ የሚገኘው የአልኮሆል መጠንዎን ከፍ ከሚያደርጉት ጥቂቶቹ ናቸው። ነገርግን የእነዚህ ተጽእኖ ሙሉ በሙሉ አይታውቁም። **በአንድ ሰዓት ውስጥ አንድ ብርጭቆ መጠጥ ቢጠጡም አልኮል በሰውነትዎ ውስጥ ሊከማች ይችላል።** ችሎታዎችና የመወሰን አቅም በዚያ አንድ ብርጭቅ መጠጥ ሊጎዳ ይችላል።

የ12 ኦንስ የጣሳ ቢራ፣ አንድ ብርጭቆ የተደባለቀ አልኮሆላዊ መጠጥና የ5 ኦንስ ብርጭቆ ዋይን፤ እነዚህ ሁሉም አንድ አይነት የአልኮሆል መጠን አላቸው።

በፍጥነት ከጠጡ ብዙ አልኮሆል ሰውነትዎ ውስጥ ይከማቻል።ሁለት ብርጭቆ መጠጥ በአንድ ሰዓት ውስጥ ከጠጡ አንዱ ሰዓት እንዳበቃ አንድ መለኪያ በደም ዝውውርዎ ውስጥ ይቀራል ማለት ነው ።

ሌሎች ነገሮችን ከግምት ሳያስገቡ እነዚህ ምሳሌዎች አንድ አሽከርካሪ ለመጠጣት ሲወስን ለምን ጊዜ ወሳኝ መሆኑን ያብራራሉ።

አንድ ሰው የሚጠጣ ሰው:

ሰባት ብርጭቆ መጠጥ በሶስት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ቢጠጣ ቢያንስ አራት (7 — 3 = 4)ብርጭቆ መጠጥ በሰውነቱ ውስጥ በ3 ሰዓቱ መጨረሻ ላይ ይቀራል። ከማሽከርከርዎ በፊት ሰውነትዎ ውስጥ የሚገኘውን አራት መለኪያ ለማስወገድ ተጨማሪ አራት ሰዓትም ቆይታ ማድረግ ያስፈልጋል።

ኮሆል መጠን



አራት ብርጭቆ መጠጥ በሁለት ሰዓት ጊዜ ውስጥ (4-2=2)በሰውነትዎ ውስጥ ቢያንስ ሁለት ብርጭቆ መጠጥ ይቀራል ማለት ነው።ከማሽከርከርዎ በፊት ቢያንስ ሌላ ሁለት መጠጡን የማስወገጃ ጊዜ ሰዓታት ያስፈልጋል ማለት ነው።

ተለቅ ያለ ሰው በሰውነቱ ውስጥ በወሰደው እያንዳንዱ የአልኮሆል መጠጥ ልክ በሰውነቱ ውስጥ አልኮሆል የማያከማችበት ጊዜያት ሊኖሩ ይችላሉ። ብዙ ደምና ሌሎች የሰውነት ፈሳሾች ቢኖራቸውም በግለሰቦች ልዩነት ምክኒያት ይህን እድል ተጠቅመን ችሎታዎችና ውሳኔዎች ተጽእኖ እንዳልደረስባቸው አድርገን ልንቀበለው አይገባም። እዚህ ላይ ተፈላጊው ጉዳይ በህጉ መሰረት ከልክ በላይ አልኮሆል ወስደዋል ወይም አልወሰዱም የሚለው አይደለም። የመወሰን ችሎታና ብቃት መጎዳት የሚጀምረው ህጋዊ ገደቡ ላይ ከመድረስዎ በፊት ነው።

አልኮሆልና ህጉ

በአብዛኛዎቹ ስቴይቶች በደም ወስጥ የሚገኘው የአልኮሆል መጠን ወይም BAC .08% ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ከመጠን በላይ እንደጠጣ ይቆጣጠራል። በሌሎቹ ስቴቶች ህጋዊ ገደቡ.10% ነው። ምን ያህል ያልጠጡ መስለዋል ወይም የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ወሳኝነት የለውም። **አብዛኛውን ጊዜ ህጋዊ** ወይም ህገወጥ አሽከርካሪ መሆንዎን የሚወስነው የትንፋሽ ወይም የሽንት ምርምራ ነው።

በአልኮሆል ተጽእኖ ስር ባሉበት ሁኔታ በማሽከርከርዎ ምክኒያት የመቆምዎ እድል ይጨምራል። በጠጡ የሞተና የሞተርሳይክል አሽከርካሪዎች በሚደርሱትን ትርጉም የለሽ ሞትና ጉዳት ምክኒያት ህግ የማስከበሩ ሁኔታ በሀገሪቱ ውስጥ እየጨመረ ነው።

የሚያስከትለው ክስ

ከአመታት በፊት የመጀመሪያ ጊዜ አጥፊዎች በትንሽ ቅጣት ወይም በአልኮሆል አብይዝ ክሳስ ላይ በመነተፍ ቅጣታቸውን የመጨረስ እድል ነበራቸው። ዛሬ የአብዛኞች ስቴቶች ህጎች ጠጥተው በሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ጠክሯል። እንዲህም የሚወስዱት እርምጃዎች መቅረት የሌለባቸው ናቸው። ይህ ማለት ዳኞች ፍርድ ይሰጡባቸዋል።

አልኮሆል ጠጥተው ወይም እጽ ወስደው በማሽከርከር ወንጀል ከተከሰሱ ከሚከተሉት ውስጥ ቅጣት ሊደርስብዎት ይችላል:

- **የመንጃ ፍቃድ መታገድ፡** የማይቀር የመንጃ ፍቃድ እገዳ የሚደርስብዎት ለፈጸሙት ወንጀል ፣ ከታሰሩ የትንፋሽ ምርመራ ለማድረግ ፍቃደኛ ካልሆኑ ነው።
- **ቅጣቶች፡** ወንጀል ቢፈጽሙ የሚሰጥ ጠንከር ያለ ቅጣት ነው።አብዛኛውን ጊዜ ከመንጃ ፍቃድ እገዳ ጋር ነውየሚበየነው።
- **የኮሚዩኒቲ ሰርቪስ፡** ከሀይዌይ ላይ የተጣለ ቆሻሻ ማንሳት፣ መኪናዎችን በሞተርሴክል ፔል ላይ ማጠብ ወይም በኢመርጀንሲ ዋርድ ላይ መስራት።
- **ክፍያ፡** ተጨማሪ የጠበቃ ክፍያ መክፈል፣ በፍርድ ቤት ውስጥ የሚጠፋው የስራ ጊዜ ወይም የአልኮሆል ኤጁኬሽን ፕሮግራምስ ላይ መሳተፍ፣ የህዝብ መጓጓዣ ዋጋዎች መንጃፍቃድዎ በታገደበት ወቅት) ተጨማሪ "የጠጣ አሽከርካሪ" ተብለው ተፈርጀው በስኑ አእምሮ የሚከፍሉት ዋጋዎች ናቸው።

አደጋዎችን መቀነስ

የማሽከርከር ችሎታዎ ምን ያህል ትክክል መሆኑን የመፍረድ ችሎታዎ በመጀመሪያ ነው የሚጠቃው። በጣም በአስዝኛ በሆነ ብቃት ቢያሽከረክሩም በጣም ጥሩ በሆነ ሁኔታ የሚያሽከረክሩ ይመስልዎታል። ውጤቱም በራስ በመተማመን ማሽከርከርና ተለቅ ተለቅ ያሉ ችግሮችን መጋፈጥ ነው። ጠጥተው የማሽከርከርን ችግርን ለመቀነስ ከመጠጣትዎ በፊት እርምጃዎች መውሰድ ነው። መጠጣትዎን ይቆጣጠሩ ወይም ማሽከርከርዎን ይቆጣጠሩ።

አይጠጡ

አይጠጡ፡ መጠጣት እንዴ ከጀመሩ የመቋቋም ሀይልዎ ይዳከማል።

ገደብ ማድረግ ወይም አካሄድዎን መቀነስ ትክክል ያልሆኑ አማራጮች ናቸው።

በአልኮሆል ከሚጠቁት ነገሮች ውስጥ አንዱ ጥሩ ውሳኔ የመወሰን ችሎታዎ ነው። በመጠኑ ለመጠጣት የሞከሩ ቢሆንም ምንያህል ችሎታዎ **በአልኮሆል ተጽእኖ እንደተዳከመ ላይታወቅዎት** ይችላል።

ወይም አያሽከርክሩ፡ መጠጣቱን ካልተቆጣጠሩ ማሽከርከርዎን መቆጣጠር ያስፈልግዎታል።

- **ሞተርሳይክሉን ይተዉት**፡ ይህን በማድረግዎም ለማሽከረክር አይፈተኑም። ወደ ቤት ለመሄድ ሌላ መንገድ ያመቻቹ።
- **ይጠብቁ**፡ የመጣጣት ልክዎን ካለፉ የሰውነትዎ አሰራር አልኮሆሉና ተያያዥ ድካሙን እስከሚያጠፋው እንዲሁም ድረስ ይጠብቁ።

ጓደኞችዎን ወደ መከላከሉ ይሸጋገሩ

ብዙ መጠጥ የጠጡ ሰዎች ሀላፊነት ያለበት ውሳኔ ለመወሰን ያስቸግራቸዋል። ሌሎቹ እርምጃ በመወሰድ ይህን ከፍተኛ አደጋ ያለበት ነገር እንዳያደርጉ ማድረግ አለባቸው። ይህንን ማድረግ ማንም ሰው **አይፈልግም**። **ምቹ አይደለም**። **አሳፋሪ ነገርና ምስጋና** የማያስገኝ ነገር ነው። ለጥረትዎ ከስንቱ አንዴ ነው ምስጋና የሚያገኙት። ነገር ግን አማራጮቹ አልፎአልፎ በጣም መጥፎ ናቸው።

ጓደኞችዎ ራሳቸውን እንዳይጎዱ የሚያደርጉበት የተለያዩ መንገዶች አሉ

- **አስተማማኝ የማሽከርከር ጊዜ ያዘጋጁ**፡ ቤታቸው እንዲደርሱ አማራጭ መንገድ ያዘጋጁላቸው።
- **የመጠጣቱን ፍጥነት ይቀንሱት**፡ በሌሎች እንቅስቃሴ እንደሚሳተፉ ያድርጓቸው።
- **ባሉበት እንዲቆዩ ያደርጓቸው**፡ ማንኛቸውንም አማራጭ ተጠቅመው ሞተርሳይክላቸው ላይ እንዳይወጡ ያድርጓቸው። ምግብና ቡና በማቅረብ ጊዜውን እንዲያሳልፉ ያደርጓቸው። ተይዞ የመታሰር፣ የመጎዳት፣ ወይም ሌላውን የመጉዳት ስጋትዎን ይግለጹላቸው። ከተቻልዎት ቁልፉን ይውሰዱባቸው።
- **ጓደኞችዎ እንዲሳተፉ ያደርጉ**፡ የጓደኞችዎን የቀረቤታ ግፊት ተጠቅመው ከጓደኞችዎ በጉዳዩ ጣልቃ እንዲገቡ ያድርጉ። ጉዳዩን ለማስተካከል ወስነው በሚገቡት ወቅት ከሌሎች ድጋፍ ለማግኘት ይችላሉ። ከጎንዎ ብዛት ያላቸው ሰዎች ካሉ እርስዎ ጠንከር ለማለት ሲችሉ አሽከርካሪው ለመቋቋም ይከብደዋል። በጊዜው ባይመሰገኑም "እንዲህ አድርጌ ብሆን ኖሮ" በማለት አይጸጸቱም።

ድካም

ሞተርሳይክል ማሽከርከር መኪና ከማሽከርከር በላይ አድካሚ ነው። በረጅም የጉዞ ወቅት በመኪና ላይ ከሚደክሙት ይልቅ በሞተር ሳይክል ይደክማሉ። በሚደክሙበት ወቅት አያሽከርክሩ። የድካም መኖር ሞተርሳይክልዎን ለመቆጣጠር አዳጋች ያደርጋዋል።

- **ራስዎን** በቶሎ ከሚያዳክሙ ነገሮች ማለትም ከንፋስ፣ ብርድ እንዲሁም ዝናብ **ይከላልከሉ**። ሙቀት የሚሰጥዎትን አልባበስ ይልበሱ።ረጅም ጉዞ የሚያሽከረክሩ ከሆነ የንፋስ መከላከያ(ዊንድ ሺልድ) ቢጠቀሙ ከሚያወጣው ዋጋ ጋር ሲተያይ የነፋስ መሆኪያ(ዊንድ ሺልድ ጥቅም ይልቃል።
- **የሚጓዙትን ርቀት ይወስኑ** ፡ ልምድ ያላቸው አሽከርካሪዎች አልፎ አልፎ በቀን ወስጥ ከስድስት ሰዓት በላይ ማሽከርከር ይሞክራሉ።
- **አዘውትረው የእረፍት ቆይታ ያድርጉ**፡ ቢያንስ በየሁለት ሰዓቱ ማሽከርከርዎን አቁመው ከሞተርሳይክልዎ ወርደው እረፍት ያድርጉ።
- **አይጠጡ ወይም እጽ አይጠቀሙ**፡ ሰው ሰራሽ ማነቃቂያ(አርቲፊሻል ስቲሙላንትስ) አቅማቸው መዳከም ሲጀምር ድካምና የአእምሮ ዝቅጠት ያስከትላሉ። አሽከርካሪዎች በእጃቸው ላይ ያለው ነገር ላይ ማትኮር አይችሉም።

14 እራስዎን ይፈትኑ

ከማሽከርከዎ በፊት አንድ መለኪያ መጠጥ ከሰውነትዎ እስኪወገድ ደረስ አንድ ሰዓት ከጠበቁ :

ሀ. ጠጥቶ በማሽከርከርዎ ምክኒያት አይታሰሩም።

ለ. የማሽከርከር ችሎታዎ አይጎዳም።

ሐ. በመጠጣትዎ ምክኒያት የሚከዙ አዳጋች ነገሮች እንዳሉ ናቸው።

መ. በቀስታ እስካሽከረከሩ ድረስ ምንም አይሆኑም።

መልስ - ገጽ40

ፍቃድዎን ማግኘት

ደህንነት ያለው ማሽከርከር እውቀትና ችሎታ ያስፈልገዋል። የመንጃፍቃድ ፈተናዎች በትራፊክ ፍሰት ወስጥ በደህንነት የማሽከርከር ችሎታዎን ብቃት የማወቂያ የበለጠው መፈተኛ ነው። የራስዎን ችሎታ መፈተሽ በቂ አይደለም። ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ችሎታቸውን ከግምት በላይ ያደርጋሉ። ጓደኞችዎና ዘመዶችዎ በአጠቃላዩ ስለችሎታዎ ትክክለኛውን ነገር በታማኝነት ይናገራሉ ማለት ከበድ ይላል። የመንጃፍቃድዎን ፈተና ገለልተኛ ውጤት ለማወቅ ይርዳል።

መንጃ ፍቃድዎን ለማግኘት የእውቀትንና በሞተርሳይክል ላይ ሆው ያልዎትን ችሎታ የሚገመግም ፈተና ማለፍ አለብዎት። የእውቀት ፈተናው በዚህ ማኑዋል(መማሪያ) መረጃ፣ ልምምድ፣ እንዲሁም ሀሳቦች ላይ የተመሳረተ ነው። የመንገድ ላይ መመሪያዎችንና ደህንነት ያለው የማሽከርከር ልምድ እንደሚያውቁና እንደሚገባዎት ማውቅ ይፈልጋሉ። በሞተርሳይክል ላይ ሆው ያልዎትን ችሎታ የሚገመግም ፈተና የትራፊክ ፍሰት ባለበት ወይም ከመንገድ ውጭ ገለል ባለ አካባቢ ይታዘዳል።

የእውቀት ፈተና

(የናሙና ጥያቄዎች)

1. የብሬክ መብራት ብልጭ ማድረግ በጣም አስፈላጊ የሚሆው:

ሀ. በጣም ተጠግቶ የሚከተልዎት ሰው ሲኖር።

ለ.በድንገት ፍጥነት በሚቀንሱበት ጊዜ

ሐ. ከፊት ለፊትዎ የማቆም ምልክት ሲኖር።

መ.የምልክት ማሳያ መብራቶች በማይሰሩበት ወቅት።

2. የፊት ብሬክ እንቅስቃሴን ለማቆም ምን ያህል የማቆሚያውን ሀይል ያጠቃልላል?

ሀ.ወደ አንድ አራተኛ የሚጠጋ

ለ. ወደ ግማሽ የሚጠጋ

ሐ. ወደ ሶስት አራተኛ

መ. አጠቃላዩን የማቆሚያ ሃይል።

3. በትክክል እየወላወሉ ለመንዳ :

ሀ. ክብደትዎን በፍጥነት ያንቀሳቅሱ

ለ. ሀንድልባርስን በፍጥነት ያዙ

ሐ . ወደ ሚዞሩበት አቅጣጫ ሀንድልባርስን ይጫኑ።

መ. ከሚዞሩበት ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ሀንድልግሪፕን ይጫኑ።

4. በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ጎማ ቢተነፍስና ማቆም ግድ ቢሆን ማድረግ ያልብዎት የበለጠ ነገር :

ሀ. ሀንድልግሪፕስን ለቀቅ አርገው ይያዝዋቸው።

ለ. ክብደትዎን ወደ ጥሩው ጎማ ያድርጉት።

ሐ. በጥሩው ጎማ ላይ ብሬክ ይያዙና ወደመንገዱ ጥግ ያሽከርክሩ።

መ. ሁለቱንም ብሬኮች ይጠቀሙና በፍጥነት ያቁሙ።

5. ከታች ያለው መኪና ወደ መጡኛው ለመዞት እየጠበቀ ነው። ማድረግ ያልብዎት የበለጠ ነገር ፣

ሀ. የአይን ግንኙነት ከመኪና ከአሽከርካሪው ጋር ያድርጉ

ለ. ፍጥነት በመቀነስ እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ ይሁኑ።

ሐ. ባልዎት ፍጥነትና ባሉበት ቦታ ይቆዩ።

መ. ባሉበት ፍጥነት ቆይተው ወደ ቀኝ ይጓዙ።

ለእራስዎን ይፈትኑ መልሶች (የበፊት ወረቀቶች)

1-ሐ	2-መ	3-መ	4-ሀ	5-ለ
6-ሐ	7-መ	8-መ	9-ሐ	10-ሐ
11-መ	12-ሀ	13-ሀ	14-ሐ	

ካላይ ላለው የእውቅት ፈተና መልሶች:

1-ለ 2-ሐ 3-ሐ 4-ሐ 5-ለ

የሞተርሳይክል ላይ የችሎታ ፈተና

መሰረታዊ የተሻከርካሪ ቁጥጥርና ግጭት የማስወገጃ ችሎታዎች የተራና የከባድ የትራፊክ ሁኔታዎችን አያያዝ ብቃትዎን ለመወሰን በሞተርሳይክል ፈተናዎች ውስጥ ተጠቃልለዋል።

ችሎታዎ ከሚፈተሯቸው ውስጥ:

- ሞተርሳይክልዎን ማወቅና **በማሽከርከር ወቅት የሚወስኑት ውሳኔዎች።**
- **ፍጥነት መጨመር፣ ብሬክና በደህንነት ማዞር።**
- **ማይት፣ መታየትና** ከሌሎች ጋር ግንኙነት ማድረግ
- **ፍጥነት ማስተካከልና** ከትራፊክ ሁኔታ ጋር ቦታዎን ማስተካከል።
- **ማቆም፣ ማዞርና፣ በፍጥነት አቅጣጫ መቀየር**
- **ከባድ ውሳኔዎችን መወሰንና መተግበር።**

ከደህንነት ጋር በተያያዘ ፈታኞቹ ነጥብ ሲሰጡ የሚከተሉት :

- ለመንቀስቀስ **የሚመርጡት** ደህነነት ያለው ፍጥነት
- ትክክለኛውን መንገድ **መመረጥና** በክልሎች ውስጥ መቆየት።
- የተለመዱና ፈጣን የማቆሞ **ማከናወን**
- የተለመዱና ፈጣን ማዞሮች ወይም ፈጣን የአቅጣጫ ለውጥ **ማከናወን**

የሞተርሳይክል መንጃ ፍቃድ ከሌሎሉ መብቱ ለማግኘት አብዮኛዎቹ ስቴቶች እንቅስቃሴው በተፈለገው ሁኔታ መተግበር አለበት።

በሞተርሳይክል ላይ ሆነው ያልዎትን ችሎታ የሚገመግም ፈተና ለሳይድካርስ ወይም ባለሶስት ጎማ ተሽከርካሪዎች የሚሆን አይደለም። እዚያ ተሽከርካሪዎች ከባለሁለት ጎማ ተሽከርካሪዎች በተለይ መልኩ ይንቀሳቀሳሉ። እንደየስቴቱ ሁኔታ ፈታኙ ለፈተና በተዘጋጀው መንገድ ላይ ሊከተልዎ ይችላል። የባለ ሁለት ጎማ ተሽከርካሪው ፈተና እስከሚጠናቀቅ እገዳዎች(በጎን የሚሄድ መኪና፣ ባለባለሶስት ጎማ ተሽከርካሪ)ሊጨመሩ ይችላሉ።

በዚህ ማኑዋል ላይ የተጠቀሙት ዲያግራሞችና ድሮዊንግስ ለማስገንዘቢያ ብቻ እንጂ ትክክለኛውን የማሽከርከሪያና የመንገድ ርቀት ለማስተካከል አይደለም።

ሞተርሳይክሎች ግንዛቤ አላቸው፤እንዲሁም የሙያ ስልጠና

ሞተርሳይክሎች ለማሽከርከር ውድ አይደሉም፣ ለመዝናናት የሚሽከረከሩ ሲሆኑ፣ እንዲሁአስፈላጊም ለማቆምም ቀላል ናቸው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን አብዛኞቹ አሽከርካሪዎች በደህንነት ለማሽከርከር የሚረዳውን ወሳኝ ችሎታ አይማሩም።

ለጀማሪዎችና ልምድ ላላቸው አሽከርካሪአች የሚሰጥ ፕሮፌሽናል ስልጠና ለገሀዱን አለም የትራፊክ ሁኔታ ያዘጋጃል። የሞተርሳይክል ፋውንዴሽን *ራይደርኮርስስ* **በሚከተሉት ላይ ችሎታዎችን ያሰተምራል፤ ያሻሽላል።**

- **ትክክለኛ ማዞር**
- የብሬኪንግ እንቅስቃሴ እንቅስቃሴ
- የመከላከያ ልባሶች ምርጫ
- መሰንክል ማስወግድ
- ትራፊክ እስትራተጂ
- ጥገና

ለመሰረታዊ ወይም ልምድ ላላቸው ራይደርኮርስ በአቅራቢያዎ ያለውን በቶል ፍሪ ይደውሉ: 800.446.9227

የሞተርሳይክል ሴፍቲ ፋውንዴሽንስ (MSF) አላማ የሞተርሳይክል አሽከርካሪዎችን ደህንነት በመንገዶችና በሃይዌዮች ላይ ማሻሻል ነው። የሞተርሳይክል ግጭቶጭንና ጎዳቶችን ለመቀንስ በሚደርገው ሙከራ ፋውንዴሽኑ በሚከተሉት ላይ ፕሮግራሞች አሉት። እነሱም ራይደር ኤጁኬሽን፣ ላይሰንሲንግ ኢምፕሩቭመንት፣ ፓብሊክ ኢንፎርሜሽንና ስታትስቲክስ ናቸው። እነዚህ ፕሮግራሞች የተዘጋጁት ለሞተርሳይክል አሽከርካሪዎችን ለመኪና አሽከርካሪዎች የተዘጋጁ ናቸው።አገረአቀፍ ኖት ፎር ዘ ፕሮፊት ኦርጋናይዜሽን፣ ዘኤም ኤስ ኤፍ በ BMW፣ Ducati፣ Harley-Davidson፣ Honda፣ Kawasaki፣ KTM፣ Piaggio/Vespa፣ Suzuki፣ Triumph፣ Victory እንዲሁም Yamaha ስፖንሰር ያደርጋሉ።

በዚህ እትም ላይ ያለው መረጃ ሞተርሳይክል የማሽከርከር ፍላጎት ያላቸውን እንዲጠቅም ነው የተሰጠው። መረጃው የተሰባሰበው ከእትሞች፣ ከቃለመጠይቆችና ስለሞተርሳይክል አጠቃቀምና ስልጠና እውቅና ካላቸው ግለሰቦችና ደርጅቶች ትዝብት ነው።በምርት አይነት ፣ በማሽከርከሩ ዘዴ፣ በፌደራል፣ በስቴትና በአካባቢ ህጎች ልዩነቶች ምክኒያት ድርጅቶችና ግለሰቦች የተለየዩ አመለካከቶች አሏቸው። በአካባቢዎ ያሉትን የሬጉላቶሪ ኢጀንሲ ስለአካባቢዎ የሞተርሳይክሎች የማሽከርከር ሁኔታ መረጃ ለማግኘት ያማክሩ። የሞተርሳይክል ሴፍቲ ፋውንዴሽንስ (MSF) ምርምር ማድረጉን ቢቀጥልም፣ የፌልድ ፊተና፣ ፓብሊሽ፣ በትምህርቱ ላይ **አስተያየቶች ቢኖሩም በዚህ ላይ ለተገለጹትን ሀሳቦች ተጠያቂነትን አይቀበልም።**

አሳታሚና አከፋፋይ
ሞተርሳይክል ሴፍቲ ፋውንዴሽን
2 Jenner Street, Suite 150, Irvine, CA 92618-3806
www.msf-usa.org

ሁለተኛ ክለሳ.....ዲሴምበር 1978
ሶስተኛ ክለሳ.....ፌብሩዋሪ 1981
አራተኛ ክለሳ.....ጀንዋሪ 1983
አምስተኛ ክለሳ.....አዞቶበር 1987
ስድስተኛ ክለሳ.....ኤፕሪል 1991
ሰባተኛ ክለሳ.....ሴፕቴምበር 1992
ስምንተኛ ክለሳ.....ጀንዋሪ 1999
ዘጠነኛ ክለሳ.....ማርች 2000
አስረኛ ክለሳ.....ጀንዋሪ 2002
አስራ አንደኛ ክለሳ.....ጁላይ 2002
አስራ ሁለተኛ ክለሳ .....ሜይ 2004
በዩ ኤስ ኤ ታተመ 00254